፫-፬-፭ ፤ ካፒቴን ፣ እስሚት ፣ ህንዶችን ፣ ያደረጋቸውን ፣ ተናገር ።
፮-፯ ፤ ፖካሆንታስ ፣ የተባለች ፣ ማንች ፣ ? ምን ፣ ሆነች ፣ ?
፰ ፤ ብራዶክ ፣ ምን ፣ ሆነ ፣ ?

## ምዕራፍ ፣ ፲፻፱ ፣ አሜሪካ ።

### ሌሎች ፣ ነገዎች ፣ ባገሩ ፣ እንዴት ፣ እንደ ፣ ገቡ ።

፩ ፤ አሁን ፣ ሌሎች ፣ እንዴት ፣ እንደ ፣ ገቡ ፣ እናገራለሁ ። በሺ ፮፻፲፫ ፣ መጀመርያ ፣ በኙዮርክ ፣ በሁድስን ፣ ወንዝ ፣ ዳር ፣ አሁን ፣ አልባኒ ፣ በቆመበት ፣ ስፍራ ፣ መግባት ፣ ተጀመረ ። የኙዮርክ ፣ ከተማ ፣ የተመሠረተው ፣ በዚያው ፣ ዘመን ፣ ነው ። ስሙንም ፣ መጀመርያ ፣ አዲሱ ፣ አምስተርዳም ፣ አሉት ። በመጀመርያ ፣ ወደ ፣ አገሩ ፣ የገቡት ፣ የሆላንድ ፣ ባላገሮች ፣ ስለ ፣ ነበሩ ፣ የዚህን ፣ ስም ፣ ከዚያ ፣ ወስደው ፣ አዲሱ ፣ አምስተርዳም ፣ ብለው ፣ ሠየሙት ።

፪ ፤ በሺ ፣ ፮፻፷፬ ፣ ደንማርኮች ፣ ይዘውት ፣ የነበሩትን ፣ የኙዮርክን ፣ አውራጃ ፣ ለእንግሊዞች ፣ አስረከቡ ። አገሩ ፣ በፍጥነት ፣ እየለማ ፣ ሄደና ፣ ከቅኝዎቹ ፣ አገሮች ፣ ኀይለኛ ፣ የተባለው ፣ እርሱ ፣ ሆነ ።

፫ ፤ በሺ ፣ ፮፻፹፩ ፣ ፔንሲልቫንያ ፣ ተያዘ ፤ አቅኚውም ፣ ዊልየም ፣ ፔን ፣ ይባላል ። እርሱም ፣ ክዌከር ፣ ከሚባል ፣ ማኅበር ፣ ወገን ፣ ነው ። ሌሎቹ ፣ ፊት ፣ እየሄዱ ፣ አገሩን ፣ ያቀኑት ፣ ሁሉ ፣ እንደርሱው ፣ የክዌከሮች ፣ ወገኖች ፣ ናቸው ። ዊልየም ፣ ፔን ፣ በመጣ ፣ ጊዜ ፣ ከህንዶቹ ፣ መሬት ፣ ገዛና ፣ ከነሱ ፣ ጋር ፣ ስምምነት ፣ አደረገ ።

፬ ፤ ይህንንም ፣ ስምምነት ፣ መቸውንም ፣ እንደ ፣ ቅዱስ ፣ ነገር ፣ አድርገው ፣ ይጠብቁት ፣ ነበር ። ስለዚህ ፣ ማንኛውም ፣ ጉዳት ፣ እንዳይደርስባቸው ፣ ይጠነቀቁላቸው ፣ ነበር ። ፔንሲልቫኒያ ፣ በሚኖሩ ፣ ክዌከርስ ፣ ላይ ፣ እንደዚህ ፣ የመሰለ ፣ ጉዳት ፣ ተደረገ ፣ የሚል ፣ ክፉ ፣ በህንዶች ፣ ታሪክ ፣ አይገኝም ።

፭ ፤ የሜሪላንድን ፣ አውራጃ ፣ ቀዳማዊ ፣ ቻርልስ ፣ ለሎርድ ፣ ባልቲሞር ፣ ሰጠው ። ይህም ፣ የሮም ፣ ካቶሊክ ፣ ነበረና ፣ በሺ ፣ ፮፻፴፬ ፣ የርሱው ፣ ሃይማኖት ፣ ያላቸውን ፣ መቶ ፣ የሚሆኑ ፣ ካቶሊኮች ፣ አምጥቶ ፣ መጀመሪያ ፣ በሜሪላንድ ፣ እንዲቀመጡ ፣ አደረገ ።

፮ ፤ ጋሮሊና ፣ መጀመርያ ፣ በሺ ፣ ፮፻፷ ፣ ተያዘ ። በሺ ፣ ፯፻፳፱ ፣ የደቡብና ፣ የሰሜን ጋሮሊና ፣ ተብሎ ፣ ተከፋፈለ ። በጂዎርጅያ ፣ መጀመሪያ ፣ ሰው ፣ የገባው ፣ በሺ ፯፻፴፫ ፣ ነው ። ያቀናው ፣ ወይም ፣ የመሠረተው ፣ ጄኔራል ፣ ጄምስ ፣ ኦግሌቶርፕ ፣ ይባላል ። ይህም ፣ ፻፲፮ ፣ ከሚሆኑ ፣ ሰዎች ፣ ጋር ፣ ከእንግሊዝ ፣ አገር ፣ መጥቶ ፣ የሰባናን ፣ ከተማ ፣ መሥራት ፣ ጀመረ ። ሌሎች ፣ አውራጃዎች ፣ የተያዙት ፣ እንግሊዝ ፣ የአሜሪካን ፣ ነጻነት ፣ ካስታወቀ ፣ በኋላ ፣ ነው ።

## ጥ ያ ቄ ።

፩ ፤ መጀመርያ ፡ በኙዮርክ ፡ ሰው ፡ የገባበት ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ?
፪ ፤ የኙዮርክ ፡ ዋና ፡ ከተማ ፡ ቀድሞ ፡ ማን ፡ ይባል ፡ ነበር ፡ ?
የኙዮርክ ፡ አውራጃ ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ?
፫ ፤ በፒንሲልቫኒያ ፡ ሰው ፡ የገባበት ፡ መቼ ፡ ነው ፡ ?
የገቡበትስ ፡ እነማን ፡ ናቸው ፡ ?
ዊልየም ፡ ፔን ፡ ህንዶችን ፡ እንደምን ፡ አኖራቸው ፡ ? ጠበቃቸውን
፬ ፤ ከነርሱ ፡ ጋር ፡ የተስማማበት ፡ ምክንያት ፡ ምንድን ፡ ነበር ፡ ?
፭ ፤ ሜሪላንድን ፡ ለሎርድ ፡ ባልቲሞር ፡ ማን ፡ ሰጠው ፡ ?
ሎርድ ፡ ባልቲሞር ፡ ማነው ፡ ?
ሜሪላንድን ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ያዘ ፡ ?
፮ ፤ በካሮሊና ፡ ምን ጊዜ ፡ ሰው ፡ ገባበት ፡ ?
ምን ፡ ጊዜ ፡ ተከፈለ ፡ ?
ጂዎርጂያ ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ተያዘ ፡ ?
የመሠረተው ፡ ማነው ፡ ?
እንዴት ፡ ያለ ፡ ከተማ ፡ ሠራ ፡ ?
ሌሎቹ ፡ አውራጃዎች ፡ እንዴት ፡ ሆኑ ፡ ?

## ምዕራፍ ፡ ፲፯ ፡ አሜሪካ ።

### ሁከት ፡ የተነሣበት ፡ ምክንያት ።

፩ ፤ በብሩንስዊክና ፡ በፍሎሪዳ ፡ መካከል ፡ ባለው ፡ የባሕር ፡ ጠረፍ ፡ ሁሉ ፡ ብዙ ፡ ሕዝቦች ፡ ገብተው ፡ እንዴት ፡ እንደ ፡ ተናኙበት ፤ የሕዝቡም ፡ ቊጥር ፡ እየበዛ ፡ እን ደሄደ ፤ እነዚህም ፡ ሁሉ ፡ ከታላቁ ፡ ብሪታንያ ፡ መንግሥት ፡ በታች ፡ እንደ ፡ ነበሩ ፡ አንባቢው ፡ በሚመጣው ፡ ምዕራፍ ፡ ሊያውቅ ፡ ይችላል ።

፪ ፤ የታላቁ ፡ ብሪታንያ ፡ ንጉሥና ፡ ሚኒስቴሮቹ ፡ የሕዝቡን ፡ መደላደልና ፡ መጠ ቀም ፡ ከተመለከቱ ፡ በኋላ ፡ ከነርሱም ፡ ጥቂት ፡ ጥቅም ፡ ለማግኘት ፡ ቊርጥ ፡ አሳብ ፡ አደረጉ ። ስለዚህ ፡ በሺ ፡ ፯፻፷፭ ፡ የቢሪትሽ ፡ ፓርላሜንት ፡ ቀረጥ ፡ ለማስከፈል ፡ ፈለገ ። ነገር ፡ ግን ፡ አሜሪኮች ፡ ገንዘባቸውን ፡ ያለፈቃዳቸው ፡ የሚወስድ ፡ ንጉሥ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ አይገኝም ፡ ብለው ፡ ቊርጥ ፡ አሳብ ፡ አድርገው ፡ ነበር ።

፫ ፤ ይህን ፡ ገንዘብ ፡ ክፈሉ ፡ የተባለውን ፡ ነቅፈው ፡ አጥብቀው ፡ ተጸየፉት ። ፓር ላሜንቱም ፡ በግድ ፡ ገንዘብ ፡ ሊያስከፍላቸው ፡ ፈለገ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ወዲያው ፡ በፍጥነት ፡ የሻይ ፡ ቀረጥ ፡ እንዲቀረጥ ፡ ተደረገ ። ቀረጡም ፡ በግድ ፡ እንዲደረግ ፡ ወደ ፡ አሜሪካ ፡ ወታደር ፡ ተላከ ።

፬ ፤ በሺ ፡ ፯፻፸፫ ፡ በነዚህ ፡ ወታደሮችና ፡ በቦስቶን ፡ ባላገሮች ፡ መኻከል ፡ ፀብ ፡ ተነሣ ። በዚህም ፡ ፀብ ፡ ውስጥ ፡ ሦስት ፡ አሜሪካኖች ፡ ተገደሉ ። አምስቱ ፡ ቈሰሉ ። ሕዝቡም ፡ በዚህ ፡ ደም ፡ መፍሰስ ፡ ሳይደነግጡ ፡ ወደፊት ፡ ለመከላከል ፡ ቈረጡ ።

፭ ፤ በሺ ፡ ፯፻፸፫ ፡ ሻይ ፡ የጫኑ ፡ መርከቦች ፡ ከሎንዶን ፡ ተነሥተው ፡ ወደ ቅኝ ፡ አገሮች ፡ ሄደው ፡ ነበር ። አንድ ፡ ሌሊት ፡ ህንዶች ፡ ተሰውረው ፡ ሄዱና ፡ እነዚህን ፡ ሻይ ፡ የጫኑ ፡ መርከቦች ፡ ወደ ፡ ባሕር ፡ ገለበጡአቸው ።

፮ ፤ ይህም ፡ ወሬ ፡ ወደ ፡ እንግላንድ ፡ በተሰማ ፡ ጊዜ ፡ ንጉሡና ፡ መኳንንቱ ፡ በጦር ፡ ኀይልና ፡ በግድ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ አሜሪኮችን ፡ ለመግዛት ፡ የማይቻል ፡ መሆኑን ፡ ተረዱት ።

## ጥያቄ ።

፩ ፤ የብሪቲሽ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ምን ፡ አደረገ ፡ ?
አሜሪኮች ፡ ምን ፡ ቍርጥ ፡ አሳብ ፡ አሰቡ ፡ ?

፪ ፤ ምን ፡ አደረጉ ፡ ? የሻይ ፡ ግብር ፡ የተባለው ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ?
ወታደሮቹ ፡ እንዴት ፡ ሆኑ ፡ ?

፫ ፤ ስለ ፡ ቦስቶን ፡ ፀብ ፡ ተናገር ።

፬ ፤ በ፲፯፻፸፫ ፡ ምን ፡ ሆነ ፡ ?
ስለ ፡ ሻይ ፡ መጥፋት ፡ ተናገር ።

፭ ፤ ንጉሡና ፡ መኳንንቱ ፡ ምን ፡ አደረጉ ፡ ?

## ምዕራፍ ፡ ፳፩ ፡ አሜሪካ ።

### ስለ ፡ አሜሪኮች ፡ ጦርነት ።

፩ ፤ የእንግሊዝ ፡ ፓርላሜንት ፡ ከፈሉ ፡ ያላቸውን ፡ ገንዘብ ፡ እንከፍልም ፡ ብለው ፡ ከኤውሮጳ ፡ የመጣውን ፡ ወታደር ፡ ለመውጋት ፡ አሜሪኮች ፡ ይሰናዱ ፡ ጀመር ። አሳባቸውን ፡ ለመፈጸም ፡ በጉባኤ ፡ የሚያስቀምጡአቸውን ፡ ሰዎች ፡ መረጡ ።

፪ ፤ መጀመርያ ፡ በሚያዝያ ፡ ፲፰ ፡ ቀን ፡ ሺ፯፻፸፭ ፡ በቦስቶን ፡ አጠገብ ፡ በሌክሲንግቶን ፡ ብዙ ፡ ደም ፡ ፈሰሰ ። ጌጅ ፡ የተባለ ፡ የእንግሊዝ ፡ ጀኔራል ፡ ከንኮርድ ፡ በተባለው ፡ ስፍራ ፡ የነበረውን ፡ ያሜሪኮችን ፡ የጦር ፡ መሣርያ ፡ ለመያዝ ፡ ስምንት ፡ መቶ ፡ ወታደሮች ፡ ሰደደ ። ነገር ፡ ግን ፡ እንግሊዝ ፡ በዙሪያው ፡ ያሉትን ፡ ሁሉ ፡ በመርከብ ፡ ጕብኝቶ ፡ ተመለሰ ።

፫ ፤ ያሜሪካም ፡ ጦር ፡ በቦስቶን ፡ ትይዩ ፡ ቦንከር ፡ በተባለ ፡ ኮረብታ ፡ ላይ ፡ ቆመ ። በዚያም ፡ ሆኑና ፡ ሥራቸውን ፡ ጀመሩ ። ወደ ፡ እንግሊዝ ፡ ምሽጎችና ፡ መርከቦች ፡

ይተኰሱባቸው፡ ጀመሩ ። እንግሊዝም፡ ገሠገሠባቸውና፡ ታላቅ፡ ውጊት፡ ከተ
ዋጉ፡ በኋላ፡ አሜሪኮችን፡ አባረሩዋቸው ። ዳሩ፡ ግን፡ እንግሊዝ፡ ብዙ፡ ወታ
ደር፡ አለቀበት ።

፬ ፡ ይህ፡ ጦርነት፡ በተደረገ፡ በሁለት፡ ሳምንት፡ ጄኔራል፡ ዋሽንግቶን፡ የተባለ፡ የአሜሪካ፡ የጦር፡ መሪ፡ ሆኖ፡ ተሾመ ።

፭ ፡ አሜሪኮችም፡ ባደረጉት፡ ነገር፡ ሁሉ፡ በጣም፡ ተበራቱና፡ በሐምሌ፡ ፬ኛ፡ ቀን፡ በሺ፡ ፯፻፸፮፡ ባንድነት፡ የተገናኙ፡ ነጻ፡ የወጣ፡ የአሜሪካ፡ መንግሥት፡ ብለው፡ አወጁ ። ይህ፡ በመደረጉ፡ ፈረንሳይና፡ እስጳንያ፡ ሆላንድም፡ ከአሜሪካ፡ ጋር፡ ጓደኝነት፡ አደረጉ ።

፮ በሺ፡ ፯፻፸፯፡ አሜሪኮች፡ ታላቅ፡ ጥቅም፡ አገኙ ። ጄኔራል፡ ቡርጎይን፡ የተባለ፡ ተከናዳ፡ ገጠማቸው ። ነገር፡ ግን፡ ወደ፡ ኋላው፡ ተመልሶ፡ በሳራቶጋ፡ ለጄኔራል፡ ጌትስ፡ እጁን፡ እንዲሰጥ፡ ግድ፡ ሆነበት ። ይህ፡ ስለ፡ ተደረገ፡ ፈረንሳዎች፡ ጦርና፡ መርከብ፡ ሰደው፡ አሜሪኮችን፡ ለመርዳት፡ ተሰናዱ ።

፯ ፡ በሺ፡ ፯፻፹፡ ከዳተኛው፡ ጄኔራል፡ አርኖልድ፡ ከእንግሊዞች፡ ጋር፡ ስለ፡ ተስማማ፡ በአሜሪኮች ላይ፡ ታላቅ፡ መከራ፡ ወደቀባቸው ። በምዕራብ፡ በኩል፡ የነበረውን፡ ታላቁን፡ ምሽጋቸውን፡ ሊሰጣቸው፡ ፈልጎ፡ ነበር ።

በዚህ፡ ምክንያት፡ ሜጀር፡ አንድሬ፡ የተባለ፡ የእንግሊዝ፡ ሹም፡ ከአርኖልድ፡ ጋር፡ ስምምነት፡ አደረገ ። እርሱንም፡ ሰላይ፡ ነው፡ ብለው፡ አሜሪኮች፡ በፍርድ፡ ቀጡት ።

፰ ፡ በዚህም፡ በሁለት፡ ወገኖች፡ መኻከል፡ ታላቅ፡ ጦርነት፡ ተደረገ ። በዚህም፡ በሁለት፡ ውጊት፡ እንግሊዞች፡ አብዛኛውን፡ አሸናፊች፡ ሁነው፡ ነበር ። ዳሩ፡ ግን፡ ይህን፡ ያህል፡ ሰፊ፡ አገር፡ የያዘውን፡ ጄኔራል፡ ለማሸነፍ፡ አልሆነላቸውምና፡ ከያዙት፡ ስፍራ፡ ላይ፡ ጥቂት፡ ጨምረው፡ በዚያው፡ ኖሩ ።

፱ ፡ የመጨረሻው፡ የእንግሊዝ፡ ተስፋ፡ የተሰጠው፡ ቬርጂኒያ፡ ውስጥ፡ በዮርክ፡ ከተማ፡ በጥቅምት፡ ፲፱፡ ቀን፡ ሺ፡ ፯፻፹፩፡ የሎርድ፡ ኮርንዎልስን፡ ወታደሮች፡ በመክበብ፡ ነበር ። ዳሩ፡ ግን፡ በውነት፡ ጦርነት፡ ሁኖ፡ እስከ፡ ሺ፡ ፯፻፹፫፡ ተዋጉና፡ ምንም፡ አልተደረገም ። ስለዚህ፡ በዚያው፡ ዘመን፡ እንግሊዝ፡ ጦሩን፡ ጠቅሎ፡ ወደ፡ አገሩ፡ ተመልሶ፡ ሄደ ።

፲ ፡ እነሆ፡ እንደ፡ ተመለከታችሁት፡ በለክሲንግቶን፡ የተጀመረው፡ ጦርነት፡ ከብዙ፡ ውጊት፡ በኋላ፡ በ፰፡ ዓመቱ፡ ተፈጸመ ።

## ጥ ያ ቄ ።

፩ ፡ አሜሪኮች፡ ምን፡ ቍርጥ፡ አሳብ፡ አሰቡ፡ ? ምን፡ አደረጉ፡ ?
የሰበሰቡት፡ ጉባኤ፡ ስም፡ ማን፡ ይባላል፡ ?
ሰዎች፡ የተመረጡት፡ ለምንድነው፡ ?

፪ ፤ መጀ መርያ፡የሰው፡ደም፡የፈሰሰበት፡ስፍራ፡ማን፡ይባላል፡?
ይኸውስ፡የሆነው፡ምን፡ጊዜ፡ነው፡?
፫ ፤ የአሜሪኮች፡ጦር፡የተሰለፈበትና ፤ የቆመበት፡ወዴት፡ነው፡?
ከዚህ፡ወዲያ፡ምን፡ሆነ፡?
፬ ፤ ዋሽንግቶን፡መሪ፡የሆነው፡ምን፡ጊዜ፡ነው፡?
፭ ፤ ጉባኤው፡ምን፡አደረገ፡?
ፈረንሳይ ፤ እስጴን ፤ ሆላንድ፡ምን፡አደረጉ፡?
፮ ፤ አሜሪኮች፡እንዴት፡ያለ፡ታላቅ፡ጠቀሜታ፡አገኙ፡?
በዚያን፡ጊዜ፡የእንግሊዞች፡ጀኔራል፡የነበረው፡ማነው፡?
፯ ፤ አሜሪኮችን፡እንዴት፡ያለ፡ችግር፡አገኛቸው፡?
የሞት፡ፍርድ፡ተፈርዶበት፡የሞተ፡የእንግሊዝ፡ሹም፡ማነው፡?
፰ ፤ ብዙ፡ጊዜ፡የተዋጉት፡ወዴት፡ነው፡?
የቀናቸው፡የትኞች፡ወገኖች፡ናቸው፡?
እንግሊዞች፡አሜሪኮችን፡ድል፡ለማድረግ፡ያገዳቸው፡ምንድነው፡?
፱ ፤ የእንግሊዞች፡የመጨረሻው፡ተስፋ፡እንዴት፡ሆነ፡?
እጁን፡የሰጠ፡የእንግሊዝ፡ጀኔራል፡እንዴት፡ያለ፡ነው፡?
ጦርነቱ፡የተጀመረው፡በየትኛው፡ውጊያ፡ነው፡?
ጦርነቱ፡ምን፡ያህል፡ጊዜ፡ወሰደ፡?

## ምዕራፍ፡፲፯፡አሜሪካ።

### ከጦርነቱ፡በኋላ፡ዩናይትድ፡እስቴትስ፡እንዴት፡እንደ ሆነ።

፩ ፤ ጦርነቱ፡ከተፈጸመ፡በኋላ፡የዩናይትድ፡እስቴትስ፡ሕዝብ፡የመንግሥቱን፡ሕግ፡ማጽናት፡አስፈላጊ፡መሆኑን፡ስለ ተረዳው፡ለጊዜው፡የሚሆነውን፡ሕግና፡ደንብ፡ባገሩ፡የተገኙ፡ጠቢባን፡አስናዱት። ይኸውም፡ደንብ፡በሺ፡፯፻፹፱፡ተቋቋመ።

፪ ፤ መልካሙና፡ደጉ፡ሰው፡ዋሽንግቶን፡መጀመርያ፡ፕሬዚዳንት፡ሆነ። በሺ፡፯፻፹፱፡ወደ፡ጽሕፈት፡ቤት፡መጣ። ከ፰፡ዓመት፡በኋላ፡እንደ፡ገና፡ተመረጠ። በሺ፡፯፻፺፱፡ሞተ። ዕድሜው፡፷፯፡ነበር። በሞቱም፡መላው፡አለቀሰለት ፤ በሺ፡፯፻፺፯፡ጆን፡አዳም፡የተባለ፡ተመረጠና፡የዩናይትድ፡እስቴትስ፡ሁለተኛው፡ፕሬዚዳንት፡ሆነ።

፫ ፤ ቀጥሎ፡ቶማስ፡ጀፈርስን፡ፕሬዚዳንት፡ሆነ። እርሱም፡በሁሉት፡ወገን፡ይሠራ፡ነበር። በሺ፡፰፻—፱፡በርሱ፡ስፍራ፡ጀምስ፡ማዲስን፡የተባለ፡ተተካ። በጀፈርስ፡አገልግሎት፡ከተደረገው፡ዋናው፡ነገር፡በሺ፡፰፻—፫፡ሉዊሳና፡የተባለው፡አውራጃ፡ከፈረንሳይ፡መግዛቱ፡ነው። ይህም፡ሰፊ፡ግዛት፡በሚሲ

ሲፒና ፣ በሮኪማውንቴን ፣ መኻከል ፣ ያለውን ፣ አገር ፣ ይጨምራል ። ይህም ፣ በ፲፭ ፣ ሚሊዮን ፣ ዶላር ፣ ተገዛ ። በማዲስን ፣ ሹመት ፣ ጊዜ ፣ በታላቁ ፣ ብሪታንያና ፣ በዩናይትድ ፣ እስቴትስ ፣ መኻከል ፣ ክፉ ፣ አኳኋን ፣ ነበር ። ትልቅ ፣ ጠላትነትም ፣ ይነሣል ፣ እየተባለ ፣ ያስፈራ ፣ ነበር ።

፬ ፤ እንዲሁም ፣ በሰኔ ፣ ፲፰ ፣ ቀን ፣ ፲፰፻፲፪ ፣ ሕዝቡ ፣ ጦርነት ፣ እንዲደረግ ፣ አወጁና ፣ ከናዳን ፣ ለመውረር ፣ ጦር ፣ ታዘዘ ። በካናዳ ፣ ወሰን ፣ ላይ ፣ አያሌ ፣ ጊዜ ፣ ግጭት ፣ ተደርጎ ፣ ነበር ። ዳሩ ፣ ግን ፣ አሜሪኮች ፣ ብዙ ፣ ጊዜ ፣ ድል ፣ ሆኑ ፣ እንጂ ፣ ያንን ፣ አውራጃ ፣ ለመያዝ ፣ አልሆነላቸውም ። ስለሆነም ፣ ያሜሪካ ፣ የጦር ፣ መርከቦች ፣ በውቅያኖስም ፣ በባሕርም ፣ አያል ፣ ጊዜ ፣ ድል ፣ አግኝተዋል ። በምድር ፣ ላይ ፣ ሲዋጉ ፣ መቸውንም ፣ እንግሊዝ ፣ ይቀናው ፣ ነበር ። ታላቅ ፣ ኀይል ፣ አድርገው ፣ በተዋጉ ፣ ጊዜ ፣ ያሜሪኮችን ፣ ዋና ፣ ከተማ ፣ ይማርኩባቸው ፣ ነበር ።

፭ ፤ በኋለኛው ፣ ጦርነት ፣ የተደረገው ፣ የኙኦርሊን ፣ ጦርነት ፣ ነው ። በጥር ፣ ፲፰ኛ ፣ ፲፰፻፲፭ ፣ የእንግሊዝ ፣ ጦር ፣ ከተማውን ፣ ለመያዝ ፣ ማለዳ ፣ ታየ ። ዳሩ ፣ ግን ፣ አሜሪኮች ፣ የመጣውን ፣ ጦር ፣ በጄኔራል ፣ ጃክስን ፣ መሪነት ፣ ክፉኛ ፣ መቱትና ፣ ወደ ፣ ኋላው ፣ ተመለሰ ፣ ከዚህ ፣ ጦርነት ፣ በኋላ ፣ ቶሎ ፣ ብለው ፣ ዕርቅ ፣ አደረጉ ። ከዚህ ፣ በኋላ ፣ ዩናይትድ ፣ እስቴትስ ፣ ተህንዶችና ፣ ተሜክሲኮች ፣ ጋር ፣ ተመዋጋት ፣ በቀር ፣ ከሌላ ፣ ጋር ፣ መዋጋቱን ፣ አቆመ ።

፮ ፤ በሺ ፣ ፰፻፲፯ ፣ ፕሬዚዳንት ፣ ማዲስን ፣ ሹመቱን ፣ ለቀቀና ፣ በስፍራው ፣ ጄምስ ፣ ሙንሮ ፣ ተሾመ ። የተከናወኑላቸው ፣ ፕሬዚዳንቶች ፣ እነዚህ ፣ ናቸው ። ጆ ፣ ክዊንኪ ፣ አዳምስ ፣ በሺ ፣ ፰፻፳፭ ። አንድሩ ፣ ጃክስን ፣ በሺ ፣ ፰፻፳፱ ፣ ተሾመ ። ይህም ፣ በሺ ፣ ፰፻፴፫ ፣ ሁለተኛ ፣ ተመረጠ ። መቫን ፣ ቡርን ፣ በሺ ፣ ፰፻፴፯ ፤ጀ ፣ ከፖልክ ፣ በሺ ፣ ፰፻፵፰ ፤ ዘ ፣ ታይሎር ፣ በሺ ፣ ፰፻፶ ፤ መ ፣ ፊልሞር ፣ በሺ ፣ ፰፻፶ ፤ ፊፒርስ ፣ ፲፰፻፶፮ ፤ ጃዝ ፣ ቡካናን ፣ በሺ ፣ ፰፻፷ ፤ አ ፣ ሊንከልን ፣ በ፲፰፻፷፩ ፣ ይህም ፣ በሺ ፣ ፰፻፷፬ ፣ እንደገና ፣ ተመረጠ ።

፯ ፤ ጥቂት ፣ ዘመናት ፣ ያህል ፣ በሰሜንና ፣ በደቡብ ፣ አሜሪካ ፣ መኻከል ፣ መከፋፋት ፣ ሆኖ ፣ ነበር ። በሺ ፣ ፰፻፷፩ ፣ የደቡብ ፣ ፲፩ ፣ መንግሥታት ፣ አንድነትን ፣ አፍርሰው ፣ ጆፈርስን ፣ ዳዊትን ፣ ፕሬዚዳንት ፣ ሾሙና ፣ ሕገ ፣ መንግሥታቸውን ፣ እንደ ፣ ዩናይትድ ፣ እስቴትስ ፣ ሕግ ፣ አደርገው ፣ አቆሙ ። የሰሜን ፣ መንግሥታት ፣ ግን ፣ ለተለያየ ፣ መንግሥት ፣ ለመገዛት ፣ አልወደዱም ። ከዚህ ፣ ወዲያ ፣ ጦርነት ፣ አበቀሉና ፣ ፬ ፣ ዓመት ፣ ተዋጉ ፣ ስምምነት ፣ ባለው ፣ መንግሥት ፣ ድል ፣ ሆኑና ፣ ጦርነቱ ፣ ተፈጸመ ። ድል ፣ ባደረጉበት ፣ ሰዓት ፣ ፕሬዚዳንት ፣ ሊንከልን ፣ ቡት ፣ የተባለ ፣ አንድ ፣ እብድ ፣ ሰው ፣ ገደለውና ፣ አንድሩ ፣ ጆንስን ፣ የተባለ ፣ ወረሰው ። ጄኔራል ፣ ኤሊሲስ ፣ የተባለ ፣ የሰሜን ፣ ጦር ፣ አዛዥ ፣ የነበረው ፣ በሺ ፣ ፰፻፷፱ ፣ ለፕሬዚዳንትነት ፣ ተመረጠ ። በሺ ፣ ፰፻፸፯ ፣ ጄኔራል ፣ ግራንት ፣ ተመለሰና ፣ በርሱ ፣ ፈንታ ፣ ሩትርፎርድ ፣ ፒ ፣ ሄይስ ፣ የተባለ ፣ ፕሬዚዳንት ፣ ለመሆን ፣ ተመረጠ ።

## ጥ ያ ቄ ።

፩ ፤ ሕገ፡ መንግሥቱ፡ የተደረገው፡ ምን፡ ጊዜ፡ ነው፡ ?

፪ ፤ የመጀመርያው፡ ፕሬዚዳንት፡ ማነው፡ ?
የመሥርያ፡ ቤቱን፡ ምን፡ ጊዜ፡ ተረከበ፡ ?
የዋሽንግቶን፡ሞት፡ ምን፡ ጊዜ፡ መሆኑ፡ ነው፡ ? በምን፡ ጠንቅ፡ ሞተ፡ ? ጆን፡ አዳም፡ ምን፡ ጊዜ፡ ተመረጠ፡ ?

፫ ፤ ጀፈርስን፡ ፈረንሳዎችን፡ በዋጋ፡ የገዛቸው፡ ምን፡ ጊዜ፡ ነው፡ ?

፬ ፤ ጦርነት፡ የታወጀው፡ ምን፡ ጊዜ፡ ነው፡ ? በካናዳ፡ እንዴት፡ ያለ፡ ጦርነት፡ ተደረገ፡ ? የበሕር፡ ላይ፡ ውጊያ፡ እንዴት፡ ሆነ፡ ? የምድሩሳ፡ ? ያዲሱ፡ ኦርሊንን፡ ጦርነት፡ ተናገር ። ጦርነት፡ የሆነው፡ መቼ፡ ነው፡ ?

፭ ፤ ሙንሮ፡ ፕሬዚዳንት፡ የሆነበት፡ ምን፡ ጊዜ፡ ነው፡ ? ከርሱ፡ የቀጠሉትን፡ ተናገር ።

፮ ፤ ስንት፡ አውራጆች፡ ተቀነሱ፡ ?
በመቀነሳቸው፡ ምን፡ ሆኑ፡ ? የኋለኛው፡ ፕሬዚዳንት፡ ማነው፡ ?

## ምዕራፍ ፤ ፫፻፫፡ አሜሪካ ።

### በዩናይትድ፡ እስቴትስ፡ ስለ፡ ተደረጉት፡ ዋና፡ ዋና፡ ታሪኮች ።

፩ ፤ ስለ፡ አሜሪካ፡ ዩናይትድ፡ እስቴትስ፡ አጭር፡ ታሪክ፡ ነገርኋችሁ ። መጀመርያ፡ ወደ፡ አሜሪካ፡ ዩናይትድ፡ አስቴትስ፡ በቬርጂኒያ፡ እየገቡ፡ የተቀመጡት፡ በሺ፡፮፻—፯፡ነበር ። ሁለተኛም፡ በኙዮርክ፡ ደች፡ የተባሉ፡ በሺ፡፮፻፳፫፡ ገቡ ። ቀየለው፡ ፑሪታን፡ ወይም፡ፒሊጋሪምስ፡ የተባሉት፡ማሳኩሲትስ፡ ፕሊማውት፡ በሚባለው፡ በሺ፡ ፮፻፴—ገቡ ።

፪ ፤ በሌሎችም፡ አውራጃዎች፡ ቶሎ፡ ብለው፡ ገቡበት ። ይበልጡንም፡ የሚበዙት፡ ከእንግሊዝ፡ አገር፡ የፈለሱት፡ ናቸው ። ከስዌድንና፡ ከጀርመን፡ ከፈረንሳይም፡ እያሉ፡ እየሄዱ፡ ገብተዋል ። እንዲሁም፡ በአትላንቲክ፡ ውቅያኖስ፡ ጠረፍና፡ አውራጃ፡ ሁሉ፡ ቀስ፡ በቀስ፡ እያሉ፡ ከውጭ፡ የገቡት፡ ሕዝብ፡ ምድረ፡ በዳውን፡ ሁሉ፡ ያዙትና፡ መከኻነኛው፡ አገር፡ ሁሉ፡ ከተማና፡ መንደሮች፡ እስኪሆን፡ ድረስ፡ በመላው፡ አገር፡ ተናኙበት ።

፫ ፤ ነገዶ፡ ሀንድ፡ በቍጥር፡ ብዙ፡ ነበሩ ። አለቆቻቸው፡ ጥቂት፡ በጥቂት፡ እያሉ፡ ከነሥራት፡ እየራቁ፡ ሄዱ ። እኩሌቶቹም፡ ታዲስ፡ ገቢዎቹ፡ ጋር፡ እየተ

ዋጉ፡ አለቁ። አኩሌቶቹም፡ ደኑ፡ እየተመነጠረ፤ ዛፉም፡ እየተቈረጠ፡ ግል
ጥልጥ፡ ሲልባቸው፡ ጊዜ፡ ተመለሱ።

፬፤ ድኾላ፤ ጐሽና፡ አጋዘን፡ እያደኑ፡ ይኖሩ፡ ነበር። አውሬዎቹ፡ ተከተማና፡
ተመንደር፡ አጠገብ፡ እየራቁ፡ ጥግ፡ እየፈለጉ፡ ሲሄዱ፡ ህንዶቹም፡ እንዲሁ፡ አብ
ረዋቸው፡ ይሄዱ፡ ነበር።

፭፤ እንዲህ፡ ብለው፡ (ሬድ፡ሜን)፡ ቀይ፡ ሰዎች፡የተባሉት፡ ከሚኖሩበት፡ አገር፡
ጠፍተው፡ ቀሩ። በምዕራብ፡ ወገን፡ አይታዩም፡ እንጂ፡ እስከ፡ ዛሬ፡ ድረስ፡
ጥቂቶች፡ አሉ። መንጋቸውና፡ ልዩ፡ ልዩ፡ የሆኑ፡ እንስሶቻቸው፡ ይገኛሉ።
አሁንም፡ የህንዶቹ፡ ቤት፡ አለ።

፮፤ ህንዶች፡ ቢመለሱም፡ በእንግሊዝ፡ ንጉሥና፡ መንግሥት፡ በታች፡ እየሆኑ፡
ነጮቹ፡ እየበዙ፡ ሄዱ። በገሩ፡ ሁከት፡ በነበረ፡ ጊዜ፡ ፫፡ሚሊዮን፡ የሚሆኑ፡
ነበሩ። መንግሥት፡ ሊያስገብራቸው፡ በፈለገ፡ ጊዜ፡ አንገብርም፡ ብለው፡ ለራ
ሳቸው፡ መንግሥት፡ አቆሙ።

፯፤ ይህም፡ መንግሥት፡ በሺ፡፲፯፻፹፱፡ ሕገ፡ መንግሥት፡ አቆመ። ይህም፡ ፫፡
ሚሊዮን፡ የሚሆን፡ ትንሽ፡ ሕዝብ፡ አሁን፡ ጠንክሮ፡ ፶፡ሚሊዮን፡ ሆኖአል።
ከነዚህ፡ ከ፶፡አንዱ፡ ባሮች፡ናቸው። ዳሩ፡ ግን፡ በሺ፡፲፰፻፷፭፡ በመንግሥታት፡
ሁሉ፡ ዘንድ፡ ባርነት፡ እንዲቀር፡ ተደርጓል። ዩናይትድ፡ እስቴትስ፡ ኮንግ
ሬስ፡ የተባለ፡ ፓርላሜንት፤ የአማካሮችና፡ የሌሎች፡ መንግሥታት፡ ቤት፡
አለው። በዋሽንግቶን፡ ቤተ፡ መንግሥት፡ የሚሰበሰቡት፡ ቀድሞ፡ ለ፬፡ዓመት፡
ይመረጡ፡ ነበር።
በኋላ፡ ለሁለት፡ ዓመት፡ ብቻ፡ ሆነ፤ መሰብሰባቸውም፡ ለመላው፡ አገር፡ የመ
ንግሥት፡ ሕግ፡ ለማውጣት፡ ነበር።

ጥያቄ።

፩፤ ቀድሞ፡ በዩናይትድ፡ እስቴትስ፡ ሰው፡ የገባው፡ ምን፡ ጊዜ፡ ነው፡?
በየት፡ ስፍራ፡ ነው፡? ቀጥሎ፡ የትኛው፡ አውራጃ፡ ተያዘ፡? ቀጥሎስ?

፪፤ በሌላው፡ አገር፡ የትኛው፡ ክፍል፡ ተያዘ፡?

፫፤ ህንዶች፡ እንዴት፡ ሆኑ፡?

፬—፭፤ የህንዶችን፡ ታሪክ፡ ተናገር። አሁን፡ የሚታዩበት፡ ወዴት፡ ነው፡?
እንዴት፡ ያሉ፡ እንስሶች፡ ይገኛሉ፡?

፮፤ ነጮች፡ በዚያ፡ እንዴት፡ ናቸው፡? በዐመፅ፡ ጊዜ፡ ስንት፡ የሚያ
ህሉ፡ ነጮች፡ ነበሩ፡?

፯፤ የአሜሪካ፡ መንግሥት፡ የተከናወነው፡ ምን፡ ጊዜ፡ ነው፡? ባሁኑ፡
ጊዜ፡ የዩናይትድ፡ እስቴትስ፡ ሕዝብ፡ ስንት፡ ይሆኑ፡? ባርነት፡ የቀረው፡
ምን፡ ጊዜ፡ ነው፡? የዩናይትድ፡ እስቴትስ፡ ምክር፡ ቤት፡ ማን፡ ይባላል።

## ምዕራፍ ፡ ፻፺፬ ፡ አሜሪካ ።

ስለ ፡ ደቡብ ፡ አሜሪካ ፡ ኤል ፡ ዶራዶና ፡ የመተደሻ ፡ ምንጭ ፡ (ማየ ፡ ተሐድሶ ።

፩ ፡ ኮሎምቡስ ፡ አሜሪካን ፡ ተማግኘቱ ፡ የሮም ፡ ጳጳስ ፡ አገሪቱን ፡ የራሱ ፡ ገንዘብ ፡ ለማድረግ ፡ ተፋለመ ። የሮሙ ፡ ጳጳስ ፡ ታልፈቀደላቸው ፡ በቀር ፡ በኤውሮጳ ፡ ያሉ ፡ ካቶሊክ ፡ የሆኑት ፡ መንግሥታት ፡ ወደዚህ ፡ አገር ፡ ገብተው ፡ የቅኝ ፡ አገር ፡ ብለው ፡ ለመያዝ ፡ አይፈቅድላቸውም ፡ ነበር ።

፪ ፡ በዚያን ፡ ዘመን ፡ ጳጳሱ ፡ ፮ኛ ፡ እስክንድር ፡ ነበር ። እርሱም ፡ በቸርነቱ ፡ ያዲሱን ፡ ዓለም ፡ እኩሌታ ፡ ለእስጳንያ ፡ ንጉሥ ፡ የቀረውን ፡ ግማሽ ፡ ለፖርቱጋል ፡ ንጉሥ ፡ ሰጠ ። እነዚህም ፡ ነገሥታት ፡ መርከቦቻቸውንና ፡ ሰዎቻቸውን ፡ እየሰደዱ ፡ አገሩን ፡ እየወጉ ፡ መጠን ፡ የሌለው ፡ የቅኝ ፡ አገር ፡ ይዘው ፡ ባላገሮቹን ፡ ባሮች ፡ አደረጉአቸው ።

፫ ፡ እስጳኞች ፡ መጀመርያ ፡ የምዕራብ ፡ ህንድ ፡ የተባለውን ፡ አውራጃ ፡ ይዘው ፡ ኩባ ፡ በሚባለው ፡ ደሴት ፡ ላይ ፡ የሀቫናን ፡ ከተማ ፡ ሠሩ ። የእስጳንያው ፡ አገረ ፡ ገዥ ፡ መኖሪያውን ፡ በዚያው ፡ አደረገ ። እነዚህኑ ፡ ደሴቶች ፡ በኋላ ፡ ሌሎች ፡ ነገዶች ፡ መጡና ፡ ያዙዋቸው ። በዚህ ፡ ዘመን ፡ ወደ ፡ አሜሪካ ፡ የሚመጡት ፡ ሁሉ ፡ ዋና አሳባቸው ፡ ወርቅና ፡ ብር ፡ ለማግኘት ፡ ነው ። ከሁሉም ፡ አብልጦ ፡ አስደናቂ ፡ ሁኖ ፡ የተነገረው ፡ ታሪክ ፡ በምዕራብ ፡ በኩል ፡ ባለው ፡ አገር ፡ መጠን ፡ የሌለው ፡ ወርቅና ፡ ብር ፡ መገኘቱ ፡ ነው ።

፬ ፡ ኤል ፡ ዶራዶ ፡ የተባለ ፡ አንድ ፡ መንግሥት ፡ ነበረ ፡ ይባላል ። የዚህም ፡ አገር ፡ ንጉሥ ፡ የወርቅ ፡ ምስል ፡ መስሎ ፡ እንዲታይ ፡ ብለው ፡ የወርቅ ፡ ዱቄት ፡ በላዩ ፡ ይነሰንሱበት ፡ ነበር ። ይህም ፡ በወርቅ ፡ የተለበጠው ፡ የንጉሥ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ በከበረ ፡ ድንጋይ ፡ በዕብነ ፡ በረድ ፡ ተሠርቶ ፡ ንጣቱ ፡ እንደ ፡ በረዶ ፡ ነበር ። የቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ ምሰሶዎች ፡ ፖርፌሪና ፡ አላባስጥር ፡ ነበሩ ። ተመግቢያው ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ዘበኞች ፡ ሁነው ፡ የሚተጉ ፡ ከወርቅ ፡ በተሠራ ፡ በወፍራም ፡ ሰንሰለት ፡ ታስረው ፡ ሁለት ፡ አንበሶች ፡ አሉበት ።

፭ ፡ አንበሶችን ፡ አልፎ ፡ አንድ ፡ ምንጭ ፡ ይታያል ። ከዚህም ፡ ከወርቅ ፡ ከተሠራ ካራት ፡ ቦምባ ፡ የሚመነጨው ፡ ውሃ ፡ ብጥብጥ ፡ ብር ፡ ይመስል ፡ ነበር ። የቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ ውስጥ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ በጽሕፈት ፡ ሊነገር ፡ አይቻልም ።

፮ ፡ ከብር ፡ የተሠራ ፡ መሠዊያ ፡ አለበት ። በዚህም ፡ ላይ ፡ ልክ ፡ የሌለው ፡ እንደ ፡ ፀሓይ ፡ የሚያበራ ፡ ወርቅ ፡ ነበረበት ። ፋኖሶቹም ፡ ዘወትር ፡ እንደ ፡ በሩ ፡ ናቸው ። ንጸብራቃቸው ፡ ከወርቅና ፡ ከብር ፡ በተሠሩ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ዕቃዎች ፡ ላይ ፡ ይብረቀረቃል ፡ ይባል ፡ ነበር ። እንዲህ ፡ እየተባለ ፡ የተነገረውን ፡ ተረት ፡ በኤውሮጳ ፡ እንደ ፡ እውነት ፡ አድርገው ፡ ያምኑ ፡ ነበር ።

፯ ፤ ኤል ፡ ዶራዶንን ፡ ለመፈለግ ፡ ብለው ፡ አያሎች ፡ ሄደዋል ። አያሎችም ፡ ይህንኑ ፡ ከወርቅ ፡ የተሠራውን ፡ መንግሥት ፡ አገኘነው ፡ ብለው ፡ አውርተዋል ። ነገር ፡ ግን ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ መንግሥት ፡ እንደሌለ ፡ እርግጥነቱ ፡ ታውቋል ።

፰ ፤ ደግሞ ፡ ሌላ ፡ ነገር ፡ እስጳኞች ፡ በአሜሪካ ፡ ለማግኘት ፡ ተስፋ ፡ አድርገውት ፡ የነበረ ፡ የመታደሻ ፡ ምንጭ ፡ የተባለውን ፡ ነበር ። ራቅ ፡ ብሎ ፡ በደኑ ፡ ጥላ ፡ ውስጥ ፡ የሚያበራ ፡ ውሃ ፡ አለ ፡ ይላሉ ። ይህም ፡ ውሃ ፡ ሲታጠቡበት ፡ የተጨማደደውን ፡ ፊት ፡ እንደ ፡ ሕፃን ፡ የሸበተውንም ፡ ጠጕር ፡ ጥቍር ፡ የሚያደርግ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ የሚያምኑ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ነው ።

## ጥያቄ

፩ ፤ የሮም ፡ ጳጳስ ፡ ምን ፡ አደረገ ፡ ?

፪ ፤ ጳጳስ ፡ እስክንድር ፡ እንዴት ፡ አደረገ ፡ ?

የእስጳንያ ፡ ንጉሥና ፡ የፖርቱጋል ፡ ንጉሥ ፡ እንደምን ፡ ሆኑ ፡ ?

ወደ ፡ አሜሪካ ፡ የመጡት ፡ ሁሉ ፡ ታላቁ ፡ አሳባቸው ፡ ምንድነው ፡ ?

ወርቅና ፡ ብር ፡ በአሜሪካ ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ?

፩—፰—፯ ስለ ፡ ኤል ፡ ዶራዶ ፡ መንግሥት ፡ እንዴት ፡ እንደ ፡ ነበሩ ፡ ተናገር ። የመታደሻ ፡ ምንጭ ፡ ስለ ፡ ተባለው ፡ ተናገር ።

## ምዕራፍ ፡ ፻፺፰ ፡ አሜሪካ ።

### የሜክሲኮች ፡ ግዛት ፡ ታሪክ ፡ ጎቲማላ ።

፩ ፡ ምንም ፡ ኤል ፡ ዶራዶ ፡ የሚባል ፡ መንግሥት ፡ በአሜሪካ ፡ ባይኖር ፡ የሜክሲኮ ፡ መንግሥት ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ ስለ ፡ ነበረው ፡ ለነዚህ ፡ ስለ ፡ ገንዘብ ፡ ለተንገበገቡ ፡ ለእስጳኞች ፡ ሕዝብ ፡ የሚበቃቸው ፡ ነበር ።

፪ ፡ ይህ ፡ አገር ፡ በአሜሪካ ፡ ደቡብ ፡ ያለውና ፡ ከሜክሲኮ ፡ ባሕር ፡ እስከ ፡ ፓስፊክ ፡ ውቅያኖስ ፡ ድረስ ፡ የዘተረጋው ፡ ክፍል ፡ ነው ። ዋና ፡ ከተማው ፡ እንደ ፡ አገሩ ፡ ሜክሲኮ ፡ ይባላል ። ይኸውም ፡ በዓለም ፡ የታወቀ ፡ ነው ።

፫ ፡ ቀድሞ ፡ አሜሪካ ፡ በተገኘ ፡ ጊዜ ፡ የሜክሲኮ ፡ ከተማ ፡ ከዛሬው ፡ ይልቅ ፡ በጣም ፡ የሚታይ ፡ ነበር ። በወርቅ ፡ ያጌጡ ፡ መቅደሶችና ፡ ቤቶች ፡ ነበሩት ። ባላገሮቹ ፡ ከሌሎች ፡ የአሜሪኮች ፡ ባላገሮች ፡ ይልቅ ፡ የሠለጠኑ ፡ ነበሩ ።

፬ ፡ በሺ ፡ ፭፻፲፱ ፡ ፈርናንዶ ፡ ኮርቴስ ፡ የተባለ ፡ እስጳንያዊ ፡ ፯፻ ፡ ሰው ፡ ይዞ ፡ ሜክሲኮን ፡ ወረራት ። የተከተሉት ፡ ሁሉ ፡ የብረት ፡ ልብስ ፡ የለበሱ ፡ ስለ ፡ ሆኑ ፡ መድፍና ፡ ጠመንጃ ፡ ባይኖራቸውም ፡ የሜክሲኮን ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ለመግጠም ፡ ሆነላቸው ።

፭ ፡ የሜክሲኮ ፡ ንጉሥ ፡ ሞንቴዙማ ፡ ይባል ፡ ነበር ። ኮርቴስን ፡ ከነሰዎቹ ፡ በታላቅ ትሕትና ፡ ተቀበላቸው ። እንዲህም ፡ ማድረጉ ፡ ከነሱ ፡ ጋር ፡ መጣላቱን ፡ ስለ ፡ አልፈለገ ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ከጥቂት ፡ ጊዜ ፡ በኋላ ፡ ኮርቴስ ፡ ሞንቴዙማን ፡ ወደ ፡ እስር ፡ ቤት ፡ አገባና ፡ በሰንሰለት ፡ አሠረው ።

፮ ፡ ሞንቴዙማ ፡ በማንኛውም ፡ ነገር ፡ ደስታ ፡ ስለሌላው ፡ ከእስጳንያ ፡ ንጉሥ ፡ በታች ፡ ለመሆን ፡ ፈቀደ ። ነገር ፡ ግን ሜክሲኮች ፡ ሁከት ፡ አነሡና ፡ ሞንቴዙማ ፡ ሕዝቡን ዝም ፡ ለማሰኘት ፡ በፈተነ ፡ ጊዜ ፡ ሰደቡት ፤ አላገጡበት ፤ ቍጣቸውም ፡ ተቃጠለ ።

፯ ፡ ስለ ፡ ተቀየሙም ፡ ጩኸትና ፡ ሽብር ፡ አስነሡና ፡ በቀስት ፡ ይናደፉ ፡ ጀመር ። እየወረወሩም ፡ የድንጋይ ፡ ነጐዴ ፡ አወረዱበት ። በምስኪን ፡ ሞንቴዙማ ፡ አንዲት ፡ ቀስት ፡ በደረቱ ፡ ስለ ፡ ተሰካችበት ፡ ወድቆ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ተንዘራጋ ። ሊጽናናም ፡ ስላ ፡ አልቻለ ፡ ይህ ፡ ያልታደለ ፡ ንጉሥ ፡ ከጥቂት ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ ሞተ ።

፰ ፡ ሜክሲኮችም ፡ የሞንቴዙማን ፡ የንጀራ ፡ ልጅ ፡ ጐቴሞዚን ፡ ዙፋኑን ፡ እንዲወርስ ፡ መረጡት ። ይህም ፡ እስጳንያዎችን ፡ በጀግንነት ፡ ገጠማቸውና ፡ ተሜክሲኮ ፡ ከተማ ፡ እየነዳ ፡ አስወጣቸው ። ነገር ፡ ግን ፡ ኮርቴስ ፡ ሌላ ፡ ጦር ፡ ይዞ ፡ መጥቶ ፡ መላውን ፡ አገር ፡ ድል ፡ አድርጎ ፡ ያዘ ።

፱ ፡ አገሩን ፡ ፈጽመው ፡ ድል ፡ እስኪያደርጉ ፡ ድረስ ፡ ኮርቴስና ፡ ወታደሮቹ ፡ ተሜክሲኮዎች ፡ ወገን ፡ የገደሉአቸው ፡ አራት ፡ ሚሊዮን ፡ ሕዝብ ፡ መሆናቸው ፡

ታወቀ ። ኮርቴን ፡ ምክንያት ፡ ሲሰጥ ፡ ሕዝቡን ፡ ወደ ፡ ክርስቲያን ፡ ሃይማኖት፡ ለመመለስ ፡ ነው ፡ እያለ ፡ ያመካኝ ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ እርሱና ፡ ወታደሮቹ፡ የሚያደርጉት ፡ የጠላትነት ፡ ሥራ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የክርስቲያን ፡ አይደለም ።

፲ ፤ ኮርቴስ አገሩን ፡ ድል ፡ አድርጎ ፡ ከያዘበት ፡ ጀምሮ ፡ እስከ፡ሺ፡፰፻፲ ፡ ድረስ፡ ሜክሲኮች ፡ የእስጳንያ ፡ ተገዢ ፡ ሁነው ፡ ኖሩና ፡ በኋላ ፡ ሁከት ፡ ተነሣ ።

፲፩ ፤ በሺ ፡ ፰፻፲፫ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አቆሙና ፡ የሜክሲኮ ፡ ሕዝብ ፡ ነጻነታቸውንና ፡ በራሳቸው ፡ አዳሪ ፡ መሆናቸውን ፡ በግልጽ ፡ አስታወቁ ። ከነዚህም ፡ አውራጃች፡ ቴክሳስ፡ የተባለው፡ አንድነት፡ ካላቸው፡ አሜሪኮች፡ ጋር፡ ተቀላቀለ።

፲፪ ፤ ጎቲማላ ፡ የተባለው ፡ አገር ፡ ሬፑብሊክ ፡ ነው ። ዋና ፡ ከተማውም ፡ ጉታማላ ፡ ይበላል ።

፲፫ ፤ ሜካሲኮ፡በላይነትን ፡ ፈልገው ፡ እየተሽቀዳደሙ ፡ ከሚመጡበት ፡ አለቆች፡ ጋር ፡ ስትታገል ፡ በደም ፡ የተለወሰች ፡ አገር፡ሆነች ። ነገር ፡ ግን ፡ በሺ ፰፻፷፫፡ የፈረንሳይ ፡ ጦር ፡ የሚባልጠውን ፡ ክፍል ፡ ድል ፡ አድርጎ ፡ ያዘና ፡ ሐምሌ ፡ ፲ኛ ፡ ቀን ፡ አላቆቹ ፡ ተፈረንሳይ ፡ ጀኔራል ፡ ጋር ፡ መከሩና ፡ ዘውዱን ፡ ለአውስትሪያ ፡ ንጉሥ ፡ ወንድም ፡ ለማክሲማሊያን ፡ ሰጡት ። እርሱም ፡ የሜክሲኮ፡ ሕዝበ ፡ ፈቅደው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እሺ ፡ እቀበላለሁ ፡ አለ ። እነርሱም ፡ ፈቃዳቸው፡ ስለ፡ሆነ፡በጥቅምት ፡ ፫ኛ ፡ ቀን ፡ ሺ ፡ ፰፻፷፫ ፡ ዘውዱን ፡ ተቀበለ ። አዲሱ፡ንጉሥ፡ ለመልካሞች ፡ ዜጎቹ ፡ እርሱም ፡ መልካም ፡ ሆነ ። ነገር ፡ ግን ፡ የፈረንሳይ ፡ ወታደሮች ፡ ከተመለሱ ፡ በኋላ ፡ ሁከት ፡ አድራጎች ፡ ተነሡና ፡ ብዙ ፡ ጭቅ ጭቅ ፡ ሆነ ። አያል ፡ ወራት ፡ ሁከት ፡ ከሆነ ፡ በኋላ ፡ የንጉሡ ፡ ወገን ፡ ድል ፡ ሆነ ። ከሌላው ፡ ይልቅ ፡ በጀኔራል ፡ ሎጵጵና ፤ በንጉሥ ፡ ማክሲሚሊያን ፡ ሸንገላ፡ ምክንያት ፡ በኤስኮፔዶ ፡ ትእዛዝ ፡ በሐምሌ ፡ ፲፱ ፡ ቀን ፡ ሺ ፡ ፰፻፷፯ ፡ ሁለቱም፡ ተገደሉ ፤ ከዚህ ፡ ወዲያ ፡ ሜክሲኮ ፡ ሬፑብሊክ ፡ ሆነ ።

## ጥያቄ ።

፩ ፤ በሜክሲኮ ፡ የወርቅ ፡ ነገር ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ?
፪ ፤ ሜክሲኮ ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ሆነ ፡ ? ዋናው ፡ ከተማ ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ?
፫ ፤ ስለ ፡ ሜክሲኮ ፡ ከተማ ፡ ተናገር ።
፬—፭ ፤ ኮርቴስ ፡ ሜባሲኮን ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ወረራት ፡? ሞንቴዙማ፡እንዴት፡ሆነ ፡?
፮ ፤ በሞንቴዙማ ፡ ምን ፡ ደረሰበት ፡ ?
፰ ፤ ኅቲሞዚን ፡ ምን ፡ አደረገ ፡ ? ኮርቴስ ፡ እንዴት ፡ አደረገ ፡ ?
፱ ፤ የኮርቴስ ፡ አሳብ ፡ ምን ፡ ነበር ፡ ?
ለክፋቱ ፡ ምን ፡ ይቅርታ ፡ አደረገ ፡ ?
፲ ፤ ሜክሲኮች ፡ ለእስጳኝ ምን ፡ ያህል ፡ ዘመን ፡ ተገዙ ፡ ?
በሺ ፡ ፰፻፲ ፡ ምን ፡ ሆነ ፡ ?
፲፩ ፤ በሺ ፡ ፰፻፲፫ ፡ ምን ፡ ሆነ ፡ ?
ቴክሳስ ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ?
፲፪ ፤ ጎቲማላ ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ?
፲፫ ፤ ሜክሲኮን ፡ ድል ፡ ያደረገ ፡ ማነው ፡? ዘውዱ ፡ ለማን ፡ ተሰጠ ፡ ?
ንጉሡ ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ? የተገደለው ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ?

## ምዕራፍ ፡ የ፺፯ ፡ አሜሪካ ።

### ስለ ፡ እስጳንያ ፡ ፔሩ ፡ አገዛዝ ።

፩ ፤ አሁን ፡ ፔሩ ፡ የተባለው ፡ አገር ፡ በሰሜን ፡ ከኤኩዋዶር ፡ ሬፑብሊክ ፡ ከምሥራቅ ፡ ከብራዚል ፤ በደቡብ ፡ ከቦልቪያና ፤ ከፓሲፊክ ፡ ውቅያኖስ ፡ ይዋሰናል ። ነገር ፡ ግን ፡ ቀድሞ ፡ ዘመን ፡ አገሩን ፡ እስጳኞች ፡ በወረሩት ፡ ጊዜ ፡ እጅግ ፡ ሰፊ ፡ ነበር ።
፪ ፤ የዚሁ ፡ አገረ ፡ ገዢ ፡ ኢንካስ ፡ ይባል ፡ ነበር ። የፔሩ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ ኢንካ ፡ የሚሉት ፡ የመጀመርያው ፡ ገዢያቸው ፡ የተወለደው ፡ ከፀሓይ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ያምናሉ ። ባላገሮቹም ፡ በፀሓይ ፡ ያመልኩ ፡ ነበር ።
፫ ፤ ፔሩ ፡ እያሉች ፡ ያማሩ ፡ ከተሞች ፡ ተሠርተውበታል ። ከሜክሲኮ ፡ ይልቅ ፡ ወርቅና ፡ ብር ፡ የሚገኘው ፡ በፔሩ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ እስጳኞች ፡ ያገሩ ፡ ጌቶች ፡ ለመሆን ፡ ቍርጥ ፡ አሳብ ፡ ነበራቸው ።
፬ ፤ መጀመርያ ፡ አገሩን ፡ የወረረው ፡ ፍራንሲስ ፡ ፒዛሮ ፡ ይባል ፡ ነበር ። በሺ ፡ ፭፻ ፴፩ ፡ ወደ ፡ ፔሩ ፡ ተጓዙና ፡ ኢንካ ፡ አታባሊፓን ፡ አሰረና ፡ በገዛ ፡ ቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ ውስጥ ፡ ቢያኖረው ፡ ከእስራት ፡ ተፈትቶ ፡ ነጻነቱን ፡ እንዲያገኝ ፡ ለፒዛሮ ፡ የሚሰጠውን ፡ በአንድ ፡ አደራሽ ፡ የሚመላ ፡ ወርቅ ፡ ቆለለ ።
፭ ፤ ይህንንም ፡ ለፒዛሮ ፡ አቀረበ ። ፒዛሮ ፡ ግን ፡ አታባሊፓን ፡ ሊገድለው ፡ አስቦ ፡ ነበርና ፡ ኢንካ ፡ ያቀረበው ፡ መዝገብ ፡ አልበቃው ፡ ብሎ ፡ ነጻ ፡ ለመልቀቅ ፡ እንቢ ፡ አለ ። እጅግም ፡ መከራ ፡ ካጸናበት ፡ በኋላ ፡ በእሳት ፡ አቃጠለው ።
፮ ፤ ፒዛሮ ፡ የፔሩን ፡ ሕዝብ ፡ ባሸነፈ ፡ ጊዜ ፡ አልማግሮ ፡ ከተባለ ፡ ከገዛ ፡ ሹሙ ፡ ጋር ፡ ጠብ ፡ አበቀለና ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ከተዋጉ ፡ በኋላ ፡ ፒዛሮም ፡ አልማግሮ ፡ ተይዞ ፡ እንዲገደል ፡ አስደረገና ፡ ወዲያው ፡ እርሱም ፡ ራሱን ፡ ገደለ ።
፯ ፤ ወዲያው ፡ ለጊዜው ፡ የፔሩ ፡ መንግሥት ፡ በብዙ ፡ አውራጃዎች ፡ የተከፈለ ፡ ሆነ ። በኋላ ፡ ግን ፡ ሁሉም ፡ ለእስጳኝ ፡ መንግሥት ፡ ስለ ፡ ተገዙ ፡ የእስጳንያ ፡ ግዛት ፡ የምዕራብ ፡ አሜሪካን ፡ አውራጃ ፡ ሁሉ ፡ ጠቅሎ ፡ ለመያዝ ፡ ጥቂት ፡ ቀረው ።
፰ ፤ ዳሩ ፡ ግን ፡ የእስጳኝ ፡ መንግሥት ፡ በነዚህ ፡ ግዛቶቹ ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ ኀይሉ ፡ እየደከመ ፡ ሄደ ። መጀመርያ ፡ ለመንግሥቱ ፡ የተደረገው ፡ መከላከል ፡ ዮሴፍ ፡ ቦናፓርቴ ፡ የእስጳኝ ፡ ንጉሥ ፡ በነበረ ፡ ጊዜ ፡ ነው ። የቀድሞው ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ወደዙፋኑ ፡ በተመለሰ ፡ ጊዜ ፡ ሕዝቡ ፡ የሚገባቸውን ፡ ለማድረግ ፡ አልተመለሱም ።
፱ ፤ አንድ ፡ ጊዜ ፡ የእስጳንያ ፡ ግዛቶች ፡ የነበሩት ፡ የአሜሪካ ፡ አውራጆች ፡ ግዛቶች ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ። አንድነት ፡ ያላቸው ፡ የሜክሲኮ ፡ መንግሥታት ፡ የመኻከል ፡ አሜሪካ ፡ ሬፑብሊክ ፡ ኙግሬናዳ ፡ ቬኔዙኤላ ፡ ኤኩዋቶር ፡ ፔሩ ፡ ቦሊቪያ ፡ ቺሊ ፡ ቢኖስ ፡ አይርስ ፡ ዑርጓዬ ፡ ፓራጓይ ።

## ጥያቄ ።

፩ ፡ ፔሩ ፡ ድል ፡ የሆነው ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ?
አሁን ፡ ፔሩ ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ?
መጀመርያ ፡ እስጳኞች ፡ በወረሩት ፡ ጊዜ ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ?
፪ ፡ የፔሩ ፡ ያገር ፡ ተወላጆች ፡ የሆኑት ፡ ገገሮቻቸው ፡ ምን ፡ ይባላሉ ፡ ? ሕዝቡስ ?
፫ ፡ ፔሩ ፡ ምን ፡ የሚገኝበት ፡ አገር ፡ ነው ፡ ?
እስጳኞች ፡ ምን ፡ አደረጉ ፡ ?
፬ ፡ ፒዛሮ ፡ ወደ ፡ ፔሩ ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ሄደ ፡ ?
ኢንካ ፡ የተባለ ፡ ማነው ፡ ? ምን ፡ አደረገ ፡ ?
፭ ፡ አታባሊፓ ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ?
፮ ፡ ፒዛሮና ፡ አልማግሮ ፡ እንዴት ፡ ሆኑ ፡ ?
ፒዛሮ ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ?
፯ ፡ የፒቪያን ፡ መንግሥት ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ?
፰ ፡ የእስጳኞች ፡ ግዛት ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ?
የእስጳንያ ፡ መንግሥት ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ? ሕዝቡ ፡ እንዴት ፡ ሆኑ ፡ ?
፱ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ እስጳኞች ፡ ይዘውት ፡ የነበረው ፡ የአሜሪካ ፡ መንግሥት ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ?

---

## ምዕራፍ ፡ ፲፯ ፡ አሜሪካ ።

### ስለ ፡ ብራዚልያን ፡ ግዛቶች ።

፩ ፣ ሰፊው ፡ አገር ፡ ብራዚል ፡ በሰሜን ፡ ወገን ፡ ከኙ ፡ ግሬናዳ ፣ ከቬኔዙኤላ ፣ ከጉዊያና ፣ በምሥራቅ ፡ ከአትላንቲክ ፡ ውቂያኖስ ፣ በደቡብ ፡ ከአትላንቲክና ፡ ከኡ ሩጓይ ፣ በምዕራብ ፡ ከቮሊቢያና ፣ ከፔሩ ፣ ኤክዋዶር ፡ ሬፑብሊክ ፡ ይዋሰናል ። ሁሉም ፡ በጠቅላላው ፡ ከዩናይትድ ፡ እስቴትስ ፡ ይሰፋል ።

፪ ፣ እስጳኞች ፡ ሌላውን ፡ የአሜሪካንን ፡ አውራጃ ፡ እየመቱ ፡ ሲይዙ ፡ ፖርቱጊሶች ፡ ወደ ፡ ብራዚልያ ፡ አቃንተው ፡ መጡና ፡ አማዞን ፡ ወንዝ ፡ አጠገብ ፡ ሲደርሱ ፡ በዚያ ፡ አውራጃ ፡ በዘመናቸው ፡ ሁሉ ፡ ውጊያ ፡ የለመዱትን ፡ ጦረኞች ፡ ሴቶች ፡ አገኙዋቸው ፡ ይባላል ።

፫ ፣ እስጳኞች ፡ እንዳደረጉት ፡ ያለ ፡ የሚያስፈራና ፡ የጭከና ፡ ሥራ ፡ ፖርቱጊ ሶች ፡ ሠርተዋል ፡ የሚል ፡ ታሪክ ፡ አላነበብንም ። ምክንያቱም ፡ የብራዚል ፡ ባላገሮች ፡ ወርቃቸው ፡ ጥቂት ፡ ስለሆነና ፡ ፖርቱጊሶችም ፡ አገሩን ፡ የቅኝ ፡ አገር ፡ ለማድረግ ፡ ስለ ፡ አሰቡት ፡ ነው ።

፬ ፣ የፖርቱጋል ፡ መንግሥት ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ ወደዚያ ፡ አገር ፡ በደለኞተን ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ አይሰድም ፡ ነበር ። በዚያን ፡ ዘመን ፡ ሰውን ፡ ወደብራ ዚል ፡ መስደድ ፡ ከዓለም ፡ ውጪ ፡ እንደ ፡ መስደድ ፡ ያለ ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ ይታሰብ ፡ ነበር ።

፭ ፣ በሺ ፡ ፭፻፵፰ ፡ ብዙ ፡ አይሁዶች ፡ ወደብራዚል ፡ ተሰደው ፡ ሄዱና ፡ በዚያ ፡ እርሻቸውን ፡ አሳምረው ፡ ሸንኮር ፡ አገዳ ፡ ስለ ፡ ተከሉ ፡ የፖርቱጋል ፡ ንጉሥ ፡ አገሩ ፡ እንደ ፡ ለማ ፡ በተመለከተ ፡ ጊዜ ፡ ከአገሩ ፡ ሀብት ፡ ድርሻውን ፡ እንዳያጣ ፡ ብሎ ፡ አገረ ፡ ገዢ ፡ የሚሆን ፡ ሹም ፡ ሾመና ፡ ሰደደ ።

፮ ፣ ፈረንሳይ ፣ እስጴን ፣ ሆላንድ ፡ ሆኑና ፡ ብራዚልን ፡ ለመያዝ ፡ ከጅለው ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ፖርቱጋል ፡ አላስነካቸውም ፣ በመጨረሻው ፡ ያገሩ ፡ ገዢ ፡ ፖርቱጋል ፡ ሆነ ። በብራዚል ፡ የተሰወረውን ፡ ሀብት ፡ ሌሎች ፡ ነገዶች ፡ ምናል ባት ፡ ዐውቀው ፡ ቢሆን ፡ ተሽቀዳድመው ፡ አገሩን ፡ ይይዙት ፡ ነበር ፡ እንጂ ፡ እን ዲህ ፡ በቀላል ፡ ባልተውትም ፡ ነበር ።

፯ ፣ ባገሩ ፡ ገብተው ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ ካለፈ ፡ በኋላ ፡ ወርቅ ፡ የሚገኝበት ፣ ጥቅም ፡ ያለ በት ፡ ስፍራ ፡ ተገኘ ። ይህም ፡ የከበረ ፡ ጥቅም ፡ ያለው ፡ ገንዘብ ፡ ከጠጠርና ፡ ካሸዋ ፡ ጋር ፡ እየተደበለቀና ፡ እየተቀላቀለ ፡ በወንዝ ፡ ውስጥ ፡ ተገኝቷል ። አንድ ፡ አንድ ፡ ጊዜም ፡ ቶጳዝና ፡ ዕንቍ ፡ የተባሉት ፡ የከበሩ ፡ ድንጋዮች ፡ ከወርቁ ፡ ጋር ፡ እየተቀ ላቀሉ ፡ ሲያብረቀርቁ ፡ ተገኝተዋል ።

፰ ፡ ምንም ፡ ሪዎ ፡ ፖርዶ ፡ የተባለው ፡ ፈሳሽ ፡ ትንሽ ፡ ቢሆን ፡ ትልቅ ፡ ዕንቍ ፡ ይገኝበታል ። ሌሎችም ፡ ወንዞች ፡ እንደዚሁ ፡ ይገኙባቸዋል ። በሮች ፡ የሆኑት ፡ ሽንቅሎች ፡ ጠጠሩንና ፡ አሸዋውን ፡ እያጠቡ ፡ እጅግ ፡ ትልቅ ፡ ዕንቍ ፡ ያገኘው ፡ ከባርነቱ ፡ ነጻ ፡ ይለቀቃል ።

፱ ፡ በሺ፡፰፻፯ ፡ የፖርቱጋል ፡ ንጉሥ ፡ ወደብራዚል ፡ ፈቀቅ ፡ አለና ፡ ቤተ ፡ መንግሥቱን ፡ ሪዎ ፡ ጃኔሮ ፡ በምትባለው ፡ ከተማ ፡ አደረገ ። ከ፲፰ ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ሊዝበን ፡ ተመለሰ ። ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ፔድሮ ፡ የተባለ ፡ ልጁ ፡ የብራዚል ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ብሎ ፡ አሳወጀ ።

፲ ፡ በሺ፡፰፻፹፩ ፡ ብራዚሎች ፡ የፔድሮ ፡ መንግሥት ፡ አይበቃንም ፡ ብለው ፡ ስለ ፡ ተቀበጠበጡ ፡ ዕሜድው ፡ ፭ ፡ ዓመት ፡ ለሆነ ፡ ሕፃን ፡ ለልጁ ፡ ዘውዱን ፡ ሰጠ ፤ ይህም ፡ ልጅ ፡ ፔድሮ ፡ ሁለተኛ ፡ ተብሎ ፡ የብራዚል ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ የሆነውና ፡ የንጉሡን ፡ ሥልጣን ፡ የአገኘው ፡ በሕፃንነቱ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ መንግሥቱ ፡ በእንደራሴ ፡ ይገዛ ፡ ነበር ።

## ጥ ያ ቄ ።

፩ ፡ የብራዚል ፡ ዳርቻ ፡ እስከየት ፡ ይሆናል ፡ ? ስፋቱስ ፡ ?
፪ ፡ ፖርቱጊሶች ፡ እንደምን ፡ ሆኑ ፡ ? አማዞን ፡ ምንድነው ፡ ?
፫ ፡ ፖርቱጊሶች ፡ እንደ ፡ እስጳኞች ፡ ጨካኞች ፡ ያልሆኑት ፡ ስለምድነው ፡ ?
፬ ፡ ወደብራዚል ፡ የሰደዳቸው ፡ ማነው ፡ ?
፭ ፡ በ፲፭፻፹፭ ፡ ምን ፡ ሆነ ፡ ? አይሁድ ፡ ምን ፡ ሆኑ ፡ ?
፮ ፡ ሌሎች ፡ አገሮች ፡ እንዴት ፡ ሆኑ ፡ ?
፯ ፡ በብራዚል ፡ ምንና ፡ ምን ፡ ተገኘ ፡ ?
፰ ፡ ሪዎ ፡ ፖርዶ ፡ ምንድነው ፡ ? ሽንቅሎች ፡ እንደምን ፡ ሆኑ ፡ ?
፱ ፡ የፖርቱጋል ፡ ንጉሥ ፡ ወደ ፡ ብራዚል ፡ የሄደው ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ? ቤተ ፡ መንግሥቱን ፡ የት ፡ ላይ ፡ አቆመ ፡ ? ወደ ፡ ሊዝበን ፡ መቼ ፡ ተመለሰ ፡ ?
ልጁ ፡ ፔድሮ ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ?
፲ ፡ በ፲፰፻፹፩ ፡ የብራዚል ፡ ሰዎች ፡ እንዴት ፡ ሆኑ ፡ ? ፔድሮ ፡ ምን ፡ አደረገ ፡ ? አሁን ፡ ብራዚል ፡ እንደምን ፡ ይገዛል ፡ ?

---

## ምዕራፍ ፡ ፻፺፫ ፡ አሜሪካ ።

### ስለ ፡ ምዕራብ ፡ ኢንዲስ ።

፩ ፤ የምዕራብ፡ኢንዲስ፡ስለ፡ተባሉት፡ደሴቶች፡ሳልተርክላችሁ፡የአሜሪካን፡ታሪክ፡ አልዘጋውም ። እነዚህ ፡ ደሴቶች ፡ በደቡብና ፡ በሰሜን ፡ አትላንቲክ ፡ ውቅያ ኖስ ፡ መኻከል ፡ የተዘረጉ ፡ ናቸው ። እነዚህም ፡ ሦስት ፡ ዘለላ ፡ ናቸው ። ባህማስ ፤ አንቲልስ ፡ ጋሪቢስ ፡ ይባላሉ ። ባህማስ ፡ የተባሉት ፡ በሰሜን ፡ በኩል ፡ ያሉት ፡ ናቸው ። ለፍሎሪዳም ፡ ይቀርባሉ ። ቍጥራቸው ፡ ፺፻ ፡ ይሆናሉ ። ከነርሱ ፡ የሚበዙት ፡ ትንንሾች ፡ ናቸው ። እነዚሁም ፡ ካሸዋና ፡ ከደንጊያ ፡ በቀር ፡ ሰው ፡ አልሰፈረባቸውም ።

፪ ፤ በነዚህም ፡ ላይ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ዐይነት ፡ የሆኑ ፡ የባሕር ፡ አሞሮች ፡ ይደርሱባቸዋል ። በበጋ ፡ ጊዜ ፡ የአሜሪካንን ፡ ባሕሮችና ፡ ጠረፎች ፡ የሚገቡኙ ፡ ብዙ ፡ አሞሮች ፡ በክረምት ፡ ጊዜ ፡ ያማሩ ፡ ማደሪያዎችና ፡ መጸጊያዎች ፡ ወደሚያገኙባቸው ፡ ወደነዚህ ፡ የተለዩ ፡ ደሴቶች ፡ ይመለሳሉ ። የባህማ ፡ ደሴቶች ፡ የታላቁ ፡ ብሪቴን ፡ ገንዘብ ፡ ናቸው ። ፴፱ሺ ፡ ባላገሮች ፡ አሉባቸው ። ዋኖቹ ፡ የተርከስ ፡ ደሴቶች ፡ ፕሮቪዲንስ ፤ ሳን ፡ ሳልባዶር ፡ ወይም ፡ ካት ፡ ደሴቶች ፡ ናቸው ። ይህ ፡ ደሴት ፡ ኰሎምቡስ ፡ መጀመርያ ፡ ያገኘው ፡ ደሴት ፡ ነው ። ባላገሮቹ ፡ ግን ፡ ጓናሀና ፡ ይሉታል ።

፫ ፤ ከምዕራብ ፡ ኢንዲስ ፡ መኻከለኛውን ፡ ክፍል ፡ በያዘው ፡ በአንቲልስ ፡ ውስጥ ፡ ኩባ ፡ የተባለው ፡ ሰፊ ፡ ደሴት ፡ ይገኛል ። ይኸውም ፡ የእስጳኞች ፡ ነው ። ነጻ ፡ የወጣው ፡ ሃይቲ ፡ ወይም ፡ ሴንት ፡ ደሚንጎ ፡ የሚባለው ፡ ደሴት ፡ በጥቍሮች ይገዛል ። ፖርቶሪኮ ፡ የእስጳኞች ፡ ነው ። ጃሚካ ፡ ጥቂቶች ፡ ትንንሾች ደሴቶችን ፡ ጨምሮ ፡ የታላቁ ፡ ብሪቴን ፡ ነው ።

፬ ፤ ካሪቢ ፡ የተባሉት ፡ ደሴቶች ፡ ብዙ ፡ ናቸው ። ያሉበትም ፡ ሌሎች ፡ ደሴቶች ፡ ካሉበት ፡ በደቡብ ፡ ምሥራቅ ፡ በኩል ፡ ከፖርቶሪኮ ፡ ክበብ ፡ አድርገው እስከ ፡ ደቡብ ፡ አሜርካ ፡ ጠረፍ ፡ ድረስ ፡ ያሉት ፡ ናቸው ። የልዩ ፡ ልዩ ፡ ኤውሮጳ ፡ መንግሥታት ፡ ገንዘብ ፡ ሁነዋል ። ከነዚህም ፡ ደሴቶች ፡ እጅግ የታወቁት ፡ ማርቲኒክ ፡ ባርባዶስ ፡ ሴንት ፡ ቶማስ ፡ ቶባጎ ፤ ሴንት ፡ ሉሲያ ፤ ሴንት ፡ ቪንሴንት ፤ ጎዋዳሎፕ ፤ አንቲጓ ፤ የሴንት ፡ ክርስቶፈር ፡ ዶሚኒካ ፤ ሳንታክሩዝ ፡ ትሪኒዳድ ፡ ናቸው ።

፭ ፤ የምዕራብ ፡ ኢንዲስ ፡ አየር ፡ ሁልጊዜ ፡ ሙቀት ፡ ነው ። በረዶና ፡ ውርጭ ፡ አይደርስበትም ። ዛፎቹ ፡ ዘለዓለም ፡ እንደ ፡ ለመለሙ ፡ ይኖራሉ ። አታክልቶችና ፡ ቍጥቋጦች ፡ ሁሉ ፡ መቸውንም ፡ በአበባ ፡ እንደ ፡ ተሸለሙ ፡ ናቸው ።

፮ ፤ የለመድናቸው ፡ ፍሬዎች ፡ እነ ፡ እነጆሪና ፡ እነ ፡ ኮክ ፡ በዚህ ፡ አገር ፡ ገና ፡ አልታወቁም ። ነገር ፡ ግን ፡ ብርቱካን ፤ በለስ ፤ ሎሚ ፡ አፕልስ ፡ ሌሎችም ፡ ጣፋጮች ፡ ፍሬዎች ሁሉ መልተዋል ።

፯ ፤ ሕዝቡ ፡ እኛ ፡ እንደምናደርገው ፡ በቆሎ ፤ ስንዴ ፤ አጃ ፡ ስናር ፡ ገብስ ፤ አይ ዘሩም ። ነገር ፡ ግን ፡ ሸንኮርአገዳ ፡ ተክለው ፡ ከዚያው ፡ ሱካር ፡ ያወጣሉ ። ቡን ፡ ጥጥ ፤ ኢንዲጎ ፡ ትንባሆ ፤ ኮኮዋ ፤ ቅመም ፡ የተባለና ፡ ሌላም ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ይዘራሉ ።

፰ ፤ በደኑ ፡ ውስጥ ፡ ማሆጋኒ ፤ ሊግኑም ፡ ቪቴ ፡ ብረት ፡ ዕንጨት ፤ ለሌላም ፡ ብልሀት ፡ የሚሆኑ ፡ ዕንጨቶች ፡ ይገኛሉ ። ከወፎችም ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ዐይነት ፡ ፓሮት ፡ ይገኛል ። ይህም ፡ ዐይነት ፡ ዎፍ ፡ በጥፍሮቹ ፡ ቆንጥጦ ፡ ከመቀመጥ ፡ ይልቅ ከሚያድርበት ፡ ቀርፎ ፡ በታች ፡ ሌሊቱን ፡ ሁሉ ፡ ራሱን ፡ ቍልቍል ፡ ዘቅዝቆና ፡ ተንጠልጥሎ ፡ ማደርን ፡ የሚወድ ፡ ነው ።

፱ ፤ በምዕራብ ፡ ኢንዲስ ፡ አራት ፡ እግር ፡ ካሉዋቸው ፡ አራዊት ፡ የሚያስገርሙት ፡ ትንንሾች ፡ ጦጣችና ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ መልክ ፡ ያላቸው ፡ እንሽላሊቶች ፡ ናቸው ። ከነዚህም ፡ ደግሞ ፡ በጣም ፡ የሚያስደንቀው ፡ እስስት ፡ ነው ። መልኩ ፡ የሚለዋወጥበትን ፡ ኀይል ፡ በፈቃድ ፡ ለማግኘት ፡ ቀድሞ ፡ የሚኖረው ፡ በአየር ፡ ይመስል ፡ ነበር ። አሁን ግን ፡ ተወደፊቱ ፡ የሚገኘውን ፡ ተንቀሳቃሽ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ እን ደሚ መገብ ፡ እርግጡ ፡ ታወቀ ። መልኩም ፡ ከሌሎች ፡ አራዊት ፡ ልዩነት ፡ የለውም ።

፲ ፤ ደግሞ ፡ የምዕራብ ፡ ኢንዲስ ፡ ሕዝብ ፡ በክረምት ፡ አይጨነቁም ። ጽኑ ፡ ነፋስ ፡ ይጐበኛቸዋል ። ይህም ፡ በድንገት ፡ ይነሣና ፡ የመርከቡን ፡ ሸራ ፡ ከደቀሉ ፡ ላይ ፡ እየቀደደ ፡ ያበላሸዋል ። ቤቱንና ፡ ዛፉንም ፡ እየገለበጠ ፡ ወደ ፡ መሬት ፡ ያጋድመዋል ።

## ጥ ያ ቄ ።

፩ ፡ የምዕራብ ፡ ኢንዲስ ፡ ደሴቶች ፡ በየት ፡ በኩል ፡ ናቸው ፡ ? ፫ ፡ ክፍል ፡
የተባሉት ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ?
የበሀማ ፡ ደሴት ፡ እንዴት ነው ፡ ?
፪ ፤ የባሕር ፡ ዳሮች ፡ የተባሉት ፡ እንዴት ፡ ያሉ ፡ ናቸው ፡ ?
በሀማኖች ፡ የማን ፡ ገንዘብ ፡ ናቸው ፡ ?
፫—፬ ፡ ዋኖቹ ፡ የትኞች ፡ ናቸው ፡ ? ስለ ፡ አንቲልስ ፡ ምን ፡ ትላለህ ፡ ? ካሪቢ ፡
የተባሉት ፡ ያሴቶች ፡ እንዴት ፡ ናቸው ፡ ?
፭ ፤ ዌስት ፡ ኢንዲስ ፡ አየሩ ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ነው ፡ ? ዋኖቹ ፡ የትኞች ፡ ናቸው ፡ ?
፮ ፤ ፍሬው ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ነው ፡ ?
፯ ፤ አገሩ ፡ ምን ፡ ያፈራል ፡ ?
፰ ፤ ደኑ ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ነው ፡ ?
ወፎችስ ፡ ? ዝንጀሮውስ ፡ ? እስስትስ ፡ ? ጽኑ ፡ ነፋስስ ፡ ?

## ምዕራፍ ፡ ፻፺፱ ፡ አሜሪካ ።

### ደግሞ ፡ ስለ ፡ ምዕራብ ፡ (ዌስት ፡ )፪ኢንዲስ ፡ ይቀጥላል ።

፩ ፤ ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ የምዕራብ ፡ ህንዶችን ፡ ብትጐበኙ ፡ አውሮጳውያን ፡ ከነዘሮቻቸውና ፡ ከብዙዎች ፡ ጥቍሮች ፡ ጋር ፡ እንዳሉ በት ፡ ታገኙዋቸዋላችሁ ። ዳሩ ፡ ግን ፡ የምዕራብ ፡ ህንዶችን ፡ ዘሮች ፡ በመኻከላቸው ፡ አንድም ፡ አታገኙ ።[እነዚያ ፡ ገና ፡ አስቀ ደሞ ፡ ጠፍተዋል ።

፪ ፤ ቀድሞ ፡ ኰሎምቡስ ፡ ከበሀማ ፡ ደሴቶች ፡ አንዱን ፡ እንዳገኘና ፡ ስሙንም ቅዱስ ፡ ሳልባዶር ፡ እንዳለው ፡ ካሁን ፡ በፊት ፡ ሰምታችኋል ። ይህም ፡ ዛሬ ፡ ካት ፡ አይላንድ ፡ የሚሉት ፡ ነው ። በዚህ ፡ ሲፍራ ፡ የተገኙትም ፡ ሕዝብ ፡ ቀድሞ በአሜርካ ፡ ይኖሩ ፡ የነበሩትን ፡ ህንዶች ፡ ይመስላሉ ።

፫ ፤ ኮሎምቡስ ፡ ሳን ፡ ሳልባዶርን ፡ አልፎ ፡ ኩባንና ፡ ሳንት ፡ ዶሚንጐን ፡ በጐ በኘ ፡ ጊዜ ፡ በነዚህ ፡ በሁለቱ ፡ ደሴቶች ፡ ብዙ ፡ ህንዶች ፡ በብዛት ፡ ይጋፉባቸው ነበር ። ኩባ ፡ ብቻ ፡ ብዙ ፡ ሚሊዮን ፡ ሕዝብ] ፡ የነበረበት ፡ ይመስላል ። አየሩ ፡ ጥሩ ፤ አገሩ ፡ ፍሬያም ፡ ነበርና ፡ የደስታ ፡ ኑሮ ፡ የሚኖሩ ፡ እንደ ፡ ነበሩ ፡ ይገልጻል ። እነዚህም ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ኋለኛው ፡ ክፋታቸው ፡ ሳይሆን ፡ በደስታ ፡ ተቀብለው በማናቸውም ፡ ረገድ ፡ በለ ፡ ኀይላቸው ፡ ረዱት ፡ እንጂ ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ አላሰቡበትም ።

፬ ፤ የምዕራብ ፡ ህንድ ፡ ደሴቶች ፡ ከተገኙ ፡ በኋላ ፡ ብዙ ፡ ዓመት ፡ ሳይቈይ ፡ ከነዚሁ ፡ ደሴቶች ፡ ያማሩትንና ፡ እጅግም ፡ ሰፊ ፡ የሆኑትን ፡ የእስጳንያ ፡ መንግሥት ፡ የራሱ ፡ ገንዘብ ፡ አደረጋቸው ። ህንዶች ፡ ጨዋነት ፡ ያላቸው ፡ ሕዝብ ፡ ስለ ፡ ሆኑ ፡ በቀላል ፡ ይገዛሉ ። እስጳኞች ፡ ግን ፡ እነዚህን ፡[እንደሚጠፉ ፡ አራዊት ፡ እንጂ ፡ እንደ ፡ ሰው ፡ አድርገው ፡ ስለ ፡ አልቈጠሩዋቸው ፡ ብዙ ፡ ሺሕ ፡ የሚሆኑትን ፡ በጠመንጃ ፡ ፈጁዋቸው ። ደግሞም ፡ በሠለጠነ ፡ ውሻ ፡ ያባርሩዋቸው ፡ ነበር ።

፭ ፤ በብዙ ፡ ደሴቶችና ፡ በየኰረፍታቸው ፡ ስር ፡ ባማሩት ፡ አውራጃዎችና ፡ በየጕ ድጓዳው ፡ አገር ፡ እንደ ፡ ንብ ፡ ይርመሰመሱ ፡ የነበሩት ፡ ሕዝብ ፡ ቍጥራቸው ፡ እጅግ ፡ አነሰ ። የተረፉትንም ፡ እንደ ፡ ባርያ ፡ አድርገው ፡ ይገዙዋቸው ፡ ነበር ። ብዙዎቹንም ፡ እግዚአብሔር ፡ የሰጣቸውን ፡ ጥሩ ፡ አየር ፡ በማጕደልና ፡ ከሥራ ፡ ብዛት ፡ የተነሣ ፡ ሕይወታቸው ፡[አቋርጦ ፡ በቶሎ ፡ እንዲጠፉ ፡ ለማድረግ ፡ ወደ ፡ ጕድ ጓድ ፡ እየገቡ ፡ እንዲሠሩ ፡ ያስገድዱዋቸው ፡ ነበር ።

፮ ፤ በእንደዚህ[ ፡ ያለ ፡ ምክንያት ፡ የምዕራብ ፡ ህንዶች ፡ ተወላጆች ፡ ስለ ፡ ጠፉ ፡ ያማረው ፡ አገራቸው ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የኤውሮጳውያን ፡ መንግሥት ፡ ገንዘብ ፡ ሁኖ ፡ ቀረ ። ኩባንና ፡ ፖርቶሪኮ ፡ የተባሉትን ፡ ደሴቶች ፡ እስጴን ፡ አጥብቆ ፡ ያዛ ቸው ፡ ጃማይካንና ፡ ቤርሙዳስን ፤ ሌሎችንም ፡ ደሴቶች ፡ ጨምሮ ፡ እንግሊዝ ፡

ያዛቸው ። ፈረንሳይም ፡ ሴንት ፡ ዶሚንጐ ፡ ማርቲኒክ ፡ ጓዳሉፕ ፡ ሰሎችንም ፡ ደሴቶች ፡ ጨምሮ ፡ ይዟል ፡ ትንንሾችም ፡ ደሴትች ፡ በሆላንዶችና ፡ በዳንማርኮች ፡ እጅ ፡ ወደቁ ።

፯ ፡ ኤውሮጳች ፡ አሜሪካንን ፡ ካገኙ ፡ በኋላ ፡ ዋና ፡ አሳባቸው ፡ ወርቅና ፡ ብር ፡ ለማግኘት ፡ ነበር ። የዚሁ ፡ አገር ፡ ተራሮችና ፡ ኮረፍቶች ፡ ሁሉ ፡ ከወርቅና ፡ ከብር ፡ የተፈጠሩ ፡ ይመስሏቸው ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ያህ ፡ ሕልም ፡ ቶሎ ፡ ብሎ ፡ ጠፋባቸው ። በምዕራብ ፡ ህንድ ፡ የሚኖሩት ፡ የህንድ ፡ ሕዝብ ፡ ወርቅና ፡ ብር ፡ ለማግኘት ፡ ብለው ፡ ወደታች ፡ በጥልቅ ፡ መሬት ፡ መቈፈራቸውን ፡ ትተው ፡ መሬት ፡ ማረስን ፡ ጀመሩ ።

፰ ፡ መሬቱም ፡ ሸንኮርአገዳ ፡ ብርቱካን ፡ ፖይን ፡ አፕልስ ፡ ሌላም ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ እንደሚሰጥ ፡ ስለ ፡ ተረዱት ፡ አሳባቸውን ፡ ወደዚህ ፡ አደረጉና ፡ ሸንቅሎችን ፡ አም ጥተው ፡ ምድሩን ፡ እንዲያርሱላቸው ፡ ለማድረግ ፡ ሰዎች ፡ ወደ ፡ አፍሪካ ፡ ተላኩ ። ብዙ ፡ ሺሕ ፡ የሚሆኑ ፡ ሸንቅሎችን ፡ አመጡና ፡ እንደ ፡ በሮች ፡ አድርገው ፡ እንዲሠሩላቸው ፡ አስገደዱአቸው ። እስካሁንም ፡ እንደ ፡ ባርያ ፡ ያሠሩዓቸው ፡ ነበር ። አሁን ፡ ግን ፡ ባሮች ፡ ነጻ ፡ ወጥተዋል ።

## ጥያቄ ።

፩ ፡ የምዕራብ ፡ ህንዶች ፡ የተባሉት ፡ እንደምን ፡ ተገዙ ፡ ?

፪ ፡ (ካት ፡ ) ድመት ፡ ደሴት ፡ የተባለውስ ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ?

ኮሎምቡስ ፡ በዚያ ፡ ያገኛቸው ፡ ሕዝብ ፡ እንዴት ፡ ያሉ ፡ ናቸው ፡ ?

፫ ፡ ቀጥሎ ፡ የትኛውን ፡ ደሴት ፡ ጐበኘ ፡ ?

ህንዶቹ እንደምን ፡ ሆኑ ፡ ?

፬-፭ ፡ የእስጳንያ ፡ መንግሥት ፡ ምን ፡ ሆነ ፡ ?

፮ ፡ እስጳኞች ፡ ህንዶችን ፡ እንደምን ፡ ያኖሩዋቸዋል ፡ ?

እስጳንያ ፡ የያዘው ፡ የትኛውን ፡ ደሴት ፡ ነው ፡ ?

እንግላንድስ ፡ ? ፈረንሳይስ ፡ ? ትንንሾቹ ፡ ደሴቶች ፡ እንዴት ፡ ሆኑ ፡ ?

፯ ፡ ኤውሮጳች ፡ ከአሜሪካ ፡ እናገኛለን ፡ ብለው ፡ የተመኙት ፡ ምንድነው ፡ ?

የጐዞአቸው ፡ ጥቅም ፡ ምንድን ፡ ሆነ ፡ ?

፰ ፡ ምን ፡ አገኙ ፡ ? ባሮች ፡ እንዴት ፡ ሆኑ ፡ ?

## ምዕራፍ ፡ ፪፪ ፡ አሜሪካ ።

### የምዕራብ ፡ እንዲስ ፡ ይቀጥላል ።

፩ ፡ በምዕራብ ፡ ህንድ ፡ የሆነውን ፡ የሚያስደንቀውን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ለመናገር ፡ አልጀምረውም ። አያሎች ፡ ደሴቶችን ፡ እጅ ፡ እየተዛወረ ፡ ገዝቶአቸዋል ። አንድ ፡ ጊዜ ፡ ላንዱ ፡ መንግሥት ፡ ተገዝተው ፡ እንደሆኑ ፡ በሌላው ፡ ጊዜ ፡ ለሌላው ፡ መንግሥት ፡ ይገዛሉ ። ብዙ ፡ ጊዜ ፡ የምድር ፡ መናወጽ ፡ ይሆንባቸዋል ። ምድሩንም ፡ ጽኑ ፡ ነፋስ ፡ በየጊዜው ፡ እየተነሣ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ያደርገዋልና ፡ ይህን ፡ አሁን ፡ ልነግራችሁ ፡ አልችልም ።

፪ ፡ የደሴቱን ፡ የሀይቲን ፡ ታሪክ ፡ ሳልመለከት ፡ አላልፈውም ፡ ይህን ፡ ያማረ ፡ ደሴት ፡ ኮሎምቡስ ፡ ወደዚህ ፡ አገር ፡ ሲመጣ ፡ አገኘውና ፡ በዚሁ ፡ ስፍራ ፡ ከሰዎቹ ፡ ጥቂቶችን ፡ አኖረ ። መጀመርያ ፡ አትላንቲክን ፡ ተሻግረው ፡ በዚህ ፡ አገር ፡ የተቀመጡ ፡ ኤሮጳውያን ፡ እነዚሁ ፡ ናቸው ። ባላገሮቹ ፡ የደሴቱን ፡ ስም ፡ ሀይቲ ፡ እስጳኞች ፡ ግን ፡ ሄስፓኜዎላ ፡ ይሉታል ። ወደ ፡ አገሩ ፡ የሚገቡት ፡ በፍጥነት ፡ እየበዙ ፡ ሄዱ ። ደሴቱ ፡ ሁሉ ፡ በፍጥነት ፡ በእስጳኞች ፡ ተያዘ ። በኋላ ፡ ቄይቶ ፡ ያገሩን ፡ ክፍል ፡ ፈረንሳይ ፡ ያዘው ። ከ፴ ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ አገሩን ፡ ፈረንሳይና ፡ እስጳንያ ፡ ተካፍለው ፡ ያዙት ።

፫ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ በዚያ ፡ ከሚኖሩት ፡ ነጮች ፡ በቍጥር ፡ ጥቍሮቹ ፡ ይበዛሉ ። በ፲፯፻፺፩ ፡ ጥቍሮቹ ፡ በጌቶቻቸው ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ ተነሡ ፡ ፈረንሳይም ፡ ሁከት ፡ አግኝቶት ፡ ነበርና ፡ ሁከቱን ፡ ለማቆም ፡ አልቻለም ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ጥቍሮቹ ፡ ልክ ፡ የሌለው ፡ ብዙ ፡ ነጭ ፡ አረዱ ፡ ቤታቸውንም ፡ እየዘረፉ ፡ አቃጠሉት ፡ የሚበዙት ፡ ነጮች ፡ ታርደው ፡ ጥቂቶች ፡ ብቻ ፡ አመለጡ ።

፬ ፡ ጥቍሮች ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ነጻ ፡ እንደ ፡ ሆኑ ፡ አሰቡና ፡ ለገዛ ፡ ራሳቸው ፡ መንግሥት ፡ ለማቆም ፡ አሰቡ ። ከልዩ ፡ ልዩ ፡ ሁከት ፡ በኋላ ፡ መላው ፡ ደሴት ፡ የሬፑብሊክ ፡ ዐይነት ፡ አቆሙ ። አለቆቹም ፡ ጥቍሮችና ፡ ወይም ፡ ክልሶቹ ፡ (ዲቃሎቹ ፡ ) ነበሩ ። እስከ ፡ ዛሬ ፡ እንዲሁ ፡ ነው ። መላው ፡ ሕዝብ ፡ በመልካም ፡ አገዛዝ ፡ ይገዛል ። የጉብኤውም ፡ ሁኔታ ፡ እየተሻሻለ ፡ ሄዶአል ። ባላገሮቹ ፡ ቅርብ ፡ ሁሉም ፡ ጥቍሮች ፡ ናቸው ፡ ለማለት ፡ ይቻላል ። ከነሱ ፡ አያሎች ፡ ብልሆች ፡ አሉ ። የግብርናና ፡ የንግድ ፡ ሌላም ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሥራ ፡ በብልሀት ፡ እያደረጉ ፡ ለመሥራት ፡ ይችላሉ ።

፭ ፡ የምዕራብ ፡ ህንዶችን ፡ ከመተዌ ፡ በፊት ፡ ስለ ፡ ቡካኔሮች ፡ ጥቂት ፡ እናገራለሁ ። ቀድሞ ፡ በ፲፮ኛው ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ በ፲፯፻፴ ፡ ከፈረንሳይና ፡ ተእንግላንድ ፡ ተጠራቅመው ፡ በምዕራቡ ፡ ጠረፍ ፡ ባለው ፡ በዶሚንጎና ፡ በዙሪያው ፡ ባሉ ፡ በቶርቱጋ ፡ ደሴቶች ፡ የታወቁት ፡ የባሕር ፡ ቀማኞች ፡ ተናኝተው ፡ ተቀምጠው ፡ ነበር ።

፮ ፡ ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ አውሬ ፡ እያደኑ ፡ ተቀመጡ ። በበዙ ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ መርከባቸውን ፡ አሰናድተው ፡ ያገኙትን ፡ ሁሉ ፡ ለመቀማት ፡ ወደባሕር ፡ ሄዱ ። ይህም ፡ ሥራ ፡ ስለተበናወነላቸው ፡ ሊሎችም ፡ ከኤወሮጳ ፡ እየመጡ ፡ ተቡካኔሮች ፡ ጋር ፡ ባንድነት ፡ ሆኑና ፡ ታላቅ ፡ መርከብ ፡ ስላ ፡ አሰናዱ ፡ ማንንም ፡ ለመቀማት ፡ ሆኑላቸው ፡ እነዚህ ፡ የባሕር ፡ ቀማኞች ፡ አያሎች ፡ ደፋሮች ፡ ገቡላቸውና ፡ አንዱን ፡ ዪፋር ፡ አለቃ ፡ አደረጉት ።

፯ ፡ በዚህ ፡ አኳኋን ፡ ቡካኔሮች ፡ አጅግ ፡ የሚያስፈሩ ፡ ሆኑ ። መርከባቸውም ፡ የነጋዶች ፡ መርከብ ፡ በሚሄድበት ፡ ዝቅ ፡ እያለ ፡ ይሄድ ፡ ጀመር ። ተሰናድቶ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ጭልፊት ፡ ከቈነጠጠ ፡ በላይ ፡ ማንም ፡ ቢመጣ ፡ ሊያስጥለው ፡ አይችልም ። መቸውንም ፡ ብዙ ፡ ሸቀጥ ፡ የያዘውን ፡ መርከብ ፡ ሲማርኩት ፡ አንድ ፡ አንድ ፡ ጊዜም ፡ ወርቅና ፡ ብር ፡ ያገኙበታል ።

፰ ፡ በእንደዚህ ፡ ያለ ፡ ሁኔታ ፡ ብዙ ፡ ሀብት ፡ አከማቹ ። አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ በነበራቸው ፡ ኀይል ፡ በታላላቅ ፡ ከተሞች ፡ ላይ ፡ አደጋ ፡ ይጥላሉ ። አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ ባላገሩን ፡ ይዘረፉሉ ። ወይም ፡ ገንዘብ ፡ አዋጥቶ ፡ እንዲሰጥ ፡ ያስገድዱታል ። ቀማኞቹ ፡ ግፍ ፡ ስለሠሩ ፡ ከዚህ ፡ ወዲያ ፡ የኤውሮጳ ፡ ነገሥታት ፡ ፍዳ ፡ ሊያስቀብሏቸው ፡ ተነሡባቸው ። በምዕራብ ፡ ህንዶች ፡ ዙሪያ ፡ ሁሉ ፡ ለማደን ፡ መርከቦችን ፡ ሰደዱ ። ተብዙ ፡ ድካም ፡ በኋላ ፡ ቡካኔሮች ፡ ጭራሽ ፡ ጠፉ ።

፱ ፡ በኋላ ፡ በምዕራብ ፡ ህንዶች ፡ ባሕ ፤ የባሕር ፡ ወንበዴዎች ፡ ተነሥተው ፡ ብዙ ፡ የንግድ ፡ መርከብ ፡ ይቀሙ ፡ ጀመር ። ዛሬውንም ፡ ቢሆን ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ሲቀሙ ፡ ይገኛሉ ።

## ጥያቄ ።

፩ ፡ በምዕራብ ፡ ህንድ ፡ ስለአሉት ፡ ጥቂቶች ፡ ደሴቶች ፡ ምን ፡ ታውቃለህ ፡ ?

፪ ፡ ሀይቲ ፡ የተባለችውን ፡ ደሴት ፡ ያገኘ ፡ ማነው ፡ ?
በዚያ ፡ ሰው ፡ እንደምን ፡ ገባ ፡ ?
ደሴቶቹ ፡ ማንና ፡ ማን ፡ ይባላሉ ፡ ?
የማን ፡ ዜጎች ፡ ናቸው ፡ ? ፍራንስስ ፡ የተባለ ፡ እንደምን ፡ ሆነ ፡ ?

፫ ፡ በ፲፮፻፺፩ ፡ ምን ፡ ተደረገ ፡ ?

፬ ፡ ሽንቅሎች ፡ እንደምን ፡ ሆኑ ፡ ? መንግሥታቸውስ ፡ ? የሰሳይቲ ፡ ደሴቶች ፡ ሁኔታ ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ?

፭ ፡ ቡካኔሮስ ፡ የተባሉ ፡ ቀማኞች ፡ እንደምን ፡ ሆኑ ፡ ?
ከጥንት ፡ የወዴት ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ ናቸው ፡ ?
ምን ፡ ጊዜ ፡ ወደዚህ ፡ ስፍራ ፡ ገቡ ፡ ?
ገብተውስ ፡ ማን ፡ በሚባል ፡ ስፍራ ፡ ተቀመጡ ፡ ?

፮ ፡ ለጊዜው ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ኖሩ ፡ ?
ከዚየስ ፡ በኋላ ፡ ምን ፡ አደረጉ ፡ ?
ከዚያስ ፡ በኋላ ፡ ከነማን ፡ ጋር ፡ ኅብረት ፡ አደረጉ ፡ ?

፯ ፡ ቡካኔሮች ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ መርከብ ፡ አሰናዱ ፡

፰ ፡ እነዚሁ ፡ የባሕር ፡ ቀማኞች ፡ ከሆኑ ፡ በኋላ ፡ ኀይላቸው ፡ እንዴት ፡ ነበር ፡ ?
በመጨረሻው ፡ እንደምን ፡ ተገዙ ፡ ?

፱ ፡ የቀሩት ፡ ሌሎች ፡ የባሕር ፡ ወንበዶች ፡ እንደምን ፡ ሆኑ ፡ ?

## ምዕራፍ ፡ ፩፻፭ ፡ ኢሺ.ያኒያ ።

### በኢሺ.ያንያ ፡ የማሊሽያን ፡ ደሴቶች ።

የእስያንና ፡ የአፍሪካን ፡ የኤውሮጳንና ፡ የአሜሪካንን ፡ ታሪክ ፡ ተርኬያለሁ ። ምናልባት ፡ አንባቢው ፡ የመላው ፡ ዓለም ፡ ታሪክ ፡ በዚሁ ፡ ብቻ የተከተተ ፡ ይመስለው ፡ ይሆናል ። ነገር ፡ ግን ፡ አንድ ፡ የአይሪሽ ሰው ፡ እንደ ፡ ተናገረው ፡ ፭ኛ ፡ ዓለም ፡ አለ ። ይህም ፡ እነሆ ፡ በጽሕፈት ፡ የምገልጠው ፡ ነው ።

፩፤ ከፓስፊክና ፡ ከህንድ ፡ ውቅያኖስ ፡ ደሴቶች ፡ ተለቅሞ ፡ ሌላ ፡ አዲስ ፡ ዓለም ፡ ስለ ፡ ተገኘ ፡ ከንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ አሜሪካ ፡ አዲስ ፡ ዓለም ፡ መባል ፡ አይገባውም ። ውቅያኖስ ፡ የተባለው ፡ ስም ፡ ለዚህ ፡ አውራጃ ፡ መሰጠቱን ፡ ነግሬአችኋለሁ ፤ ደሴቶቹ ፡ ሁሉ ፡ ባንድነት ፡ ቢሰበሰቡ ፡ አራት ፡ ሚሊዮን ፡ እስኩዬር ፡ ማይል ፡ የሚሆነውን ፡ መሬት ፡ ሊከድኑት ፡ ይችላሉ ።

፪፤ ሦስት ፡ ክፍል ፡ የሆኑ ፡ ውቅያኖሶች ፡ አሉ ። ለእስያ ፡ የብስ ፡ የቀረቡ ፡ ሁነው ፡ በህንድ ፡ ውቅያኖስ ፡ ላይ ፡ የተጋደሙት ፡ ደሴቶች ፡ ማሊሲያ ፡ ይባላሉ ። ከነዚህም ፡ ታላላቆቹ ፡ ቦርኖ ፡ ሱማትራ ፤ ጃቫ ፡ ናቸው ።

በደሴቱ ፡ ላይ ፡ ያሉት ፡ ባላገሮች ፡ ያለፈውን ፡ ታሪካቸውን ፡ የማያውቁ ፡ ያባቶቻቸውንም ፡ ታሪክ ፡ ለማሰብ ፡ ምኞት ፡ የሌላቸው ፡ ስለ ፡ ሆኑ ፤ ስለ ፡ ማሊሲያ ፡ የተጻፈው ፡ ታሪክ ፡ እጅግ ፡ ጥቂት ፡ ነው ።

፫፤ ቁም ፡ ነገር ፡ የለበትም ፡ እንጂ ፡ የጃቩ ፡ ታሪክ ፡ ይልቅ ፡ የተሻለ ፡ ሁኖ ፡ ታውቋል ። ይህንንም ፡ ደሴት ፡ በሺ ፡ ፭፻፲ ፡ ፖርቱጋሎች ፡ በአገኙት ፡ ጊዜ ፡ በጣም ፡ ለም ፡ ነበር ። የሱካር ፡ አገዳ ፤ ቡን ፤ ሩዝ ፡ በርበሬ ፤ ቅመም ፤ ሌላም ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ ፍሬ ፡ ሁሉ ፡ ተገኝቶበታል ። ደግሞም ፡ ወርቅና ፡ ብር ፡ ሌላም ፡ የከበረ ፡ ደንጊያ ፡ ሁሉ ፡ ይገኝበት ፡ ነበር ።

፬፤ የደሴቱ ፤ ርዝመት ፡ ፯፻፶ ፡ ማይል ፡ ይሆናል ። ወዲያው ፡ እንደ ፡ ተገኘ ፡ ሰፊውን ፡ ክፍል ፡ ሆላንዶች ፡ ያዙትና ፡ ከደሴቱ ፡ በሰሜን ፡ ጠረፍ ፡ ወገን ፡ ባታቪያ ፡ የተባለውን ፡ ከተማ ፡ ሠሩ ።

፭፤ ከተማው ፡ በረባዳው ፡ መሬት ፡ ረግረግ ፡ ካለበት ፡ ላይ ፡ ተሠርቶአል ። በቦይ ፡ የሚሄድ ፡ የረጋ ፡ ውሃ ፡ በየመንገዱ ፡ ላይ ፡ ይገኛል ። (ይታያል ፡) ከሕንፃው ፡ ማማር ፡ የተነሣ ፡ ከተማዪቱን ፡ ባታቪያን ፡ የምሥራቅ ፡ ንግሥት ፡ ይሉዋታል ። በቦዩና ፡ በጐዳናው ፡ ላይ ፡ የዛፍ ፡ ጥላ ፡ ስለሚወድቅበት ፡ ለከተማዪቱ ፡ ውበትና ፡ ማማር ፡ ሰጥቶአታል ።

፮፤ በሺ ፡ ፯፻፹ ፡ የሕዝቡ ፡ ብዛት ፡ እስከ ፡ ፻፷ ፡ ሺሕ ፡ ደርሶ ነበር ። ከልዩ ፡ ልዩ ፡ ዓለም ፡ የመጡ ፡ ሕዝብ ፡ በመኻከላቸው ፡ ይኖራሉ ። ከነዚሁ ፡ ውስጥ ፡

በቍጥር ፤ የሚያንሱት ፡ ኤውሮጳውያን ፡ ናቸው ፡ ነገር ፡ ግን ፡ መንግሥቱም ፡ በኤውሮጳውያኖች ፡ እጅ ፡ ነው ።

፰ ፤ አየሩ ፡ ለጤና ፡ የማይበማማ ፡ ስለሆነ ፡ ባታቪያ ፡ እያደር ፡ በፍጥነት ፡ እየተ ዋረደች ፡ ሄደች ። ተውጭ ፡ አገር ፡ የሚመጡት ፡ ሕዝብ ፡ በሚያስፈራ ፡ ንዳድ ይታመሙ ፡ ጀመር ። አንዳንድ ፡ ጊዜስ ፡ ከቶውንም ፡ መርከበኞቹ ፡ ሁሉ ፡ በበ ሽታ ፡ እያለቁ ፡ መርከቢቱ ፡ ባዶዋን ፡ ትቀራለች ።

፱ ፤ ከሺ ፡ ፰፻፲፩ ፡ እስከ ፡ ሺ ፡ ፰፻፲፮ ፡ የጃቫን ፡ ደሴት ፡ እንግሊዝ ፡ ያዘና ፡ በኋላ፡ ለቀድሞዎቹ ፡ ገዥዎች ፡ መለሰላቸው ። ሆላንዶችም ፡ ታላቅ ፡ ገዥ ፡ በባላገሮቹ ፡ ላይ ፡ ሾሙባቸው ፡ ይባላል ። የሕዝቡም ፡ ብዛት ፡ ፲፯ ፡ ሚሊዮን ፡ ናቸው ።

ጥ ያ ቄ ።

፩ ፤ በውቅያኖስ ፡ ያሉ ፡ ደሴቶች ፡ ኦሺያኒያ ፡ የተባሉ ፡ እንዴት ፡ ያሉ ፡ ናቸው ፡ ? የነዚሁ ፡ ኦሺያኒያ ፡ የተባሉ ፡ ስፋት ፡ እንዴት ፡ ይሆናል ፡ ?

፪ ፤ ማሊሲያ ፡ የተባለው ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ነው ፡ ? ባላገሮቹ ፡ እንዴት ፡ ያሉ ፡ ናቸው ፡ ?

፫ ፤ ጃቫ ፡ የተባለው ፡ ደሴት ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ነው ፡ ? የተገኘው ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ?

ምን ፡ ያፈራል ፡ ? ማዕድን ፡ ይገኝበታልን ፡ ?

፭ ፤ የጃቫ ፡ ስፋት ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ይሆን ፡ ? ባታቪያን ፡ ማን ፡ ሠራው ፡ ?

፮ ፤ የከተማውን ፡ ሁኔታ ፡ ተናገር ።

፯ ፤ በ፲፯፻፹ ፡ የባታቪያ ፡ ሕዝብ ፡ ብዛት ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ኑሮዋል ፡ ?

፰ ፤ ቀድሞ ፡ ከተማው ፡ እንዴት ፡ ነበር ፡ ? አየሩስ ፡ ? በ፲፰፻፲፩ ፡ ምን ፡ ሆነ ፡ ? በ፲፰፻፲፮ ፡ ደግሞ ፡ ምን ፡ ሆነ ? ደች ፡ የተባሉ ፡ ማለት ፡ ሆላንዶች ፡ እንዴት ፡ ሆኑ ፡ ?

## ምስራፍ ፡ ፪፻፱ ፡ አሺያኒያ ።

### የኦሺያኒያ ፡ ክፍል ፡ አውስትራላያን ፡

፩ ፤ የአሺያኒያ ፡ ፪ኛው ፡ ክፍል ፡ አውስትራልያ ፡ ይባላል ። ይህም ፡ አውስትራልያ ፡ ኒጊኒ ፤ ቫን ፡ ዳይምንስላድንና ፡ በዙሪያው ፡ ያሉትንም ፡ ሌሎች ፡ ደሴቶች ፡ ሁሉ ፡ ይጨምራል ። አውስትራልያ ፡ አንድ ፡ እጅግ ፡ ሰፊ ፡ የሆነ ፡ ደሴት ፡ ነው ። ስፋቱ ፡ ሦስት ፡ ሚሊዮን ፡ እስኩዬር ፡ ማይል ፡ ይሆናል ። ይኸውም ፡ በስፋት ፡ ኤውሮጳን ፡ ያህላል ።

፪ ፤ የጥንቱ ፡ የአውስትራልያ ፡ ተወላጆች ፡ በዓላም ፡ ካሉት ፡ ሕዝብ ፡ እጅግ ፡ የተዋረዱ ፡ ናቸው ። ጥቍሮች ፡ ናቸው ። እግሮቻቸውና ፡ እጆቻቸው ፡ ቀጫጭኖች ፡ ናቸው ። መልካቸውም ፡ ከዝንጀሮ ፡ ወገን ፡ ይመስላል ። በማማራቸውም ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ በብልሀታቸው ፡ በማሊሲያን ፡ ደሴቶች ፡ ከሚገኙት ፡ አውራንግ ፡ አውታንግ ፡ ከሚባሉት ፡ አይበልጡም ።

፫ ፤ ይህን ፡ ታላቅ ፡ ደሴት ፡ በሺ ፡ ፮፻፮ ፡ ያገኙት ፡ ሆላንዶች ፡ ናቸው ። አሁን ፡ ግን ፡ መላው ፡ በታላቁ ፡ ብሪቴን ፡ ይገዛል ። ካፒቴን ፡ ጄምስ ፡ ኩክ ፡ የተባለ ፡ የታወቀ ፡ መርከበኛ ፡ ከሺ ፡ ፯፻፸ ፡ ጀምሮ ፡ እንደያዘው ፡ ነበር ።

፬ ፤ አሁን ፡ ግን ፡ አውራጃው ፡ አምስት ፡ ዘንድ ፡ ተከፍሎአል ። እነርሱም ፡ ኙሳውት ፤ ዌልስ ፤ ቢክቶሪያ ፤ ክዊንስላንድ ፤ ደቡብ ፡ አውስትራልያ ፤ የምዕራብ ፡ አውስትራልያ ፡ ናቸው ። ኙሳውት ፡ ዌልስ ፡ የቀድሞ ፡ ነው ። በሺ ፡ ፯፻፹፰ ፡ ወደዚያ ፡ መግባት ፡ ተጀመረ ። ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ ቦታኒቤ ፡ ተባለ ።

፭ ፤ ቀድሞ ፡ የነበሩት ፡ ሕዝብ ፡ የሚከበሩ ፡ ሕዝብ ፡ አልነበሩም ። የእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ በደለኞቹን ፡ ወደ ፡ ቅጣት ፡ ወይም ፡ እስራት ፡ ከማግባት ፡ ይልቅ ፡ ወደ ፡ ኙሳውት ፡ ዌስት ፡ ለመስደድ ፡ አሰበ ። እንዲሁም ፡ በየዓመቱ ፡ ብዙ ፡ ነገር ፡ የተጫኑ ፡ መርከቦች ፡ ወደዚያ ፡ ይሄዱ ፡ ነበር ።

፮ ፤ ይህም ፡ አሳብ ፡ እንደ ፡ ብርቱ ፡ ቅጣት ፡ ተብሎ ፡ ታሰበ ። ይህ ፡ ኙሳውት ፡ ዌስት ፡ የተባለ ፡ አገር ፡ በጣም ፡ ለም ፡ ነው ። አየሩም ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ እንግሊዝ ፡ በብልሀት ፡ አድርጎት ፡ ያሆናል ። ደጎች ፡ ሰዎች ፡ ሁነው ፡ ሳሉ ፡ ችግረኞች ፡ የሆኑትን ፡ ሠርተው ፡ እንዲያድሩ ፡ ብሎ ፡ የሰደዳቸው ፡ ይመስላል ።

፯ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ በዚያ ፡ ባዲሱ ፡ ቅኝ ፡ አገር ፡ የነበሩት ፡ ሰዎች ፡ ፈጽሞ ፡ ቁም ነገራሞችና ፡ እውነተኞች ፡ ብቻ ፡ ነበሩ ። ከባላገሮቹም ፡ ጥቂቶቹ ፡ በደለኛ ፡ ሆኖ ፡ መገኘት ፡ እንደ ፡ ነውር ፡ ሆኖ ፡ ይሰማቸው ፡ ነበር ። ይኸውም ፡ ጐረቤቶቻቸው ፡ እንደነርሱ ፡ ክፉዎች ፡ እንደ ፡ ነበሩ ፡ ስለ ፡ ዐወቁ ፡ ነው ።

፰ ፤ በኋላ ፡ ሕዝቡ ፡ መሻሻል ፡ ጀመሩ ። የበደለኞችም ፡ ልጆች ፡ አደጉ ፤ ወላጆቻቸውም ፡ መልካም ፡ አደርገው ፡ አስተማሩዋቸው ።
፱ ፤ ባዲሱ ፡ ሆላንድ ፡ አገር ፡ የተወለደች ፡ አንዲት ፡ ሴት ልጅ ፡ ወደ ፡ እንግላንድ ፡ ለመመለስ ፡ ትወድ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ብለው ፡ ቢጠይቋት ፡ «እንኳን ፡ አልመለስም ፤ በዚያ ፡ ሕዝቡ ፡ ሌቦች ፡ ናቸው ና ፡ ወደዚያ ፡ መመለስ ፡ አፈራለሁ» ፡ አለች ። መርከብ ፡ በመጣ ፡ ቍጥር ፡ ሌባ ፡ እየተባለ ፡ ከእንግላንድ ፡ አያል ፡ ሰው ፡ ሲመጣ ፡ አይታለችና ፡ ተእንግላንድ ፡ የሚመጣው ፡ ሁሉ ፡ ሌባ ፡ ይመስላት ፡ ነበር ።
፲ ፤ በደለኞች ፡ እየተባሉ ፡ የሚመጡት ፡ አዘውትረው ፡ ይመጡ ጀመሩ ። ሌላ ፡ መኖሪያ ፡ እስከሚያስፈልጋቸው ፡ ድረስ ፡ የሚመጡት ፡ ቍጥር ፡ እየበዛ ፡ ሄደ ። በሺ ፡ ፲፯፻፺፰ ፡ አያሎችን ፡ ወደ ፡ ኙሳውት ፡ ዌልስ ፡ በመርከብ ፡ ወሰዱአቸው ። ሕዝቡም ፡ በሺ ፡ ፲፰፻፵ ፡ ከነበረው ፡ መቅሠፍት ፡ ዳኑ ። በሺ ፡ ፲፰፻፸፯ ፡ የታረሰው ፡ ምድር ፡ ስፋት ፡ ፳፻ሺ ፡ ኤክር ፡ መሬት ፡ ነው ። ወርቅ ፡ የሚያወጡበት ፡ አርባ ፡ ጕደጓድና ፡ መደብ ፡ እርሳስ ፤ ቆርቆሮ ፤ ብር ፡ የሚገኝባቸው ፡ አያሎች ፡ ጕድጓዶች ፡ ነበሩ ። በሺ ፡ ፲፰፻፸፯ ፡ የሕዝቡ ፡ ቍጥር ፡ ፯፻፰፱ሺ ፡ ሆነው ፡ ነበር ።
፲፩ ፤ በሺ ፡ ፲፰፻፶፱ ፡ የተከፋፈለ ፡ አውራጃ ፡ ሁኖ ፡ እስቲቆም ፡ ድረስ ፡ ክዊንስላንድ ፡ ከኙሳውት ፡ ዌልስ ፡ የተከፈለ ፡ አገር ፡ ነው ። የሰሜን ፡ ምሥራቅ ፡ አውስትራልያን ፡ የብስና ፡ በካርፔንታሪያ ፡ ባሕር ፡ ዙሪያ ፡ ያሉትን ፡ ደሴቶች ፡ ሁሉ ፡ ይጨምራል ። ስፋቱም ፡ ፯፻፰፱ ፡ ሺ ፡ እስኴር ፡ ማይል ፡ ይሆናል ።
፲፪ ፤ አውራጃው ፡ ለእርሻ ፡ የተስማማ ፡ ነው ። ከሰልና ፡ ሌላም ፡ ከመሬት ፡ የሚወጣ ፡ ነገር ፡ ይገኝበታል ። አየሩ ፡ መልካም ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ለእንግሊዝ ፡ ሥራ ፡ የሚሆን ፡ ጥጥ ፡ የሚሰጥ ፡ አገር ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም ።

## ጥያቄ ።

፩ ፤ አውስትራልያ ፡ ምን ፡ ይባላል ፡ ? ያዲሱ ፡ ሆላንድ ፡ ስፋት ፡ የቱን ፡ ያህላል ፡ ?
፪ ፤ ባላገሮች ፡ እንዴት ፡ ያሉ ፡ ናቸው ፡ ?
፫ ፤ አዲሱ ፡ ሆላንድ ፡ የተገኘው ፡ መቼ ፡ ነው ፡ ? ያገኘውስ ፡ ማነው ፡ ?
አሁን ፡ በማን ፡ እጅ ፡ ነው ፡ ? ማን ፡ ይዘታል ፡ ?
ካፒቴን ፡ ኩክ ፡ የተባለ ፡ የያዘው ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ኖሮአል ፡ ?
፬ ፤ ያዲሱ ፡ ሆላንድ ፡ ሦስት ፡ ቅኝ ፡ አገሮች ፡ እነማን ፡ ናቸው ፡ ?
ኙሳውት ፡ ዌልስ ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ተያዘ ፡ ? ያገሩን ፡ መያዝ ምን ፡ አሉት ፡ ?
፭ ፤ መጀመርያ ፡ የገቡት ፡ ማን ፡ ይባላሉ ፡ ? በየዓመቱ ፡ ከእንግሊዝ ፡ አገር ፡ ወደቦታኒቤ ፡ የሚላኩት ፡ ምን ፡ የሆኑ ፡ ሰዎች ፡ ናቸው ፡ ?
፮ ፤ በአገሩ ፡ የገቡት ፡ እነዚሁ ፡ ምን ፡ ይነገርላቸዋል ፡ ?
፯ ፤ በኋለኛው ፡ ዘመን ፡ እንዴት ፡ ሆኑ ፡ ?

፱ ፤ ስለ ፡ አንዲት ፡ ያዲሱ ፡ ሆላንድ ፡ ተወላጅ ፡ የነበረች ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ተናገር ።

፲ ፤ በደለኞች ፡ ወደ ፡ ደቡብ ፡ ዌልስ ፡ ከተላኩ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ጊዜ ፡ ሆነ ፡ ? ለእርሻ ፡ የሚሆን ፡ ምን ፡ ያህል ፡ መሬት ፡ ይገኛል ፡ ? ማዕድን ፡ ይገኛልን ፤ ? የሕዝቡ ፡ ብዛት ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ይሆናል ፡ ?

፲፩ ፤ ክዊንስላንድ ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ነው ፡ ? ስፋቱ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ነው ፤ ? ምን ፡ ያፈራል ፡ ?

---